ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የዳውሮ ብሔረሰብ የ"Tookki -Be'aa" (ቶክ-ቤኣ) ወይም ዘመን መለወጫ በዓል የክወና ስርዓት ትንተና

ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ለማሟያነት የቀረበ ጥናት፤

በ

አፈወርቅ ማኖሶ

ሰኔ፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# የዳውሮ ብሔረሰብ የ"Tookki -Be’aa" (ቶክ-ቤኣ) ወይም ዘመን መለወጫ በዓል የክወና ስርዓት ትንተና

በ

አፈወርቅ ማኖሶ

አማካሪዎች፡- ማንያለው አባተ (ዶ/ር)

ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ለማሟያነት የቀረበ ጥናት፤

ሰኔ፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

**የዳውሮ ብሔረሰብ የ"Tookki -Be'aa" (ቶክ-ቤኣ) ወይም ዘመን መለወጫ በዓል የክወና ስርዓት ትንተና ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤**

በ

አፈወርቅ ማኖሶ

የአማካሪ ስም፡-____________________________ ፊርማ፡-____________________

የውስጥ ፈታኝ ስም፡-____________________________ፊርማ፡-__________________

የውጭ ፈታኝ ስም፡-____________________________ ፊርማ፡-__________________

# ምስጋና

ይህ የጥናት ሥራ ከግብ እስኪደርስ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ከትልመ ጥናት እስከ ዋናው ጥናት ድረስ ላማከሩኝ ዋና አማካሪዬ ማንያለው አባተ (ዶ/ር) እና ለረዳት አማካሪዬ ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር) ከልብ የመነጨ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ፡፡

በመቀጠል በተለያዩ ጊዜያት ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመቀበል በሚሰለች መልኩ ቤታቸውና ሥራ ቦታቸው ስመላለስ እንኳ ሳይሰላቹ ለጥናት የሚሆኑ በርካታ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ ለመረጃ አቃባዮቼ ልባዊ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

በመጨረሻ ይህንን የጥናት ጽሑፍ በምሰራበት ጊዜ የተለያዩ ሀሳቦችን በማጋራት ጥናቱ ለዚህ ደረጃ እንዲደርስ ላደረጉ ለቤተሰቦቼና ለጓደኞቼ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ላቀርብ እፈልጋለሁ፡፡

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ "በዳውሮ ብሔረሰብ ዘንድ የሚከበረውን (Tookki -Be'aa) (ቶክ-ቤኣ) ወይም ዘመን መለወጫ በዓል ክወና ሥርዓትን መተንተን" ነበር፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት የመስክ ምልከታ፣ የሰነድ ፍተሻ እና የቃለ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ጥናቱ ገላጭ ተንታኝ የጥናት ንድፍን ተከትሎ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ከመረጃ ሰጪዎች ተሰብስበው በአይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ከመረጃ ሰጪዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ከትርጉም አንጻር "ቶክ-ቤኣ" ማለት ጥሬ ትርጉም ተሸክሞ ማየት ወይም መዝኖ ማየት ማለት እንደሆነና ለዚህም ሲባል ሰውና እንስሳትን ጨምሮ ጠግበው በልተው እንደሚያድሩና ቤት ውስጥ ያሉ ሁሉም የቤት ዕቃዎች በምግብና በመጠጥ ተሞልተው የሚያድሩ መሆኑን ውጤቱ ያሳያል፡፡ በዓሉ ሰዎች በጋራ ሆነው የሚያከብሩት ሲሆን በዓሉን ምክንያት በማድረግ የተለያዩ ባህላዊና ማህበራዊ ክዋኔዎች የሚፈጸሙ እንደሆነም ከውጤቱ መረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ ማጠቃለያ፣ ግኝቶችና የዳውሮ ብሔረሰብ በየዓመቱ ቶክ-ቤኣን (አዲሱን ዓመት) ሲያከብሩ ከበዓሉ ጋር የማይነጣጠሉ በርካታ ባህላዊ እና ማህበራዊ እንዲሁም ትዕምርታዊ ጉዳዮች የሚከወኑ መሆናቸው ታውቆ ለበዓሉ ተገቢ እውቅና በሚመለከታቸው አካላት ሊሰጥ እንደሚገባና ሌሎችም አስተያየቶች በአጥኚው ተሰጥተው ጥናቱ ተቋጭቷል፡፡*

ማውጫ


ይዘት ገጽ

ምስጋና……………………………………………………………………..i

አጠቃሎ……………………………………………………………………ii

በጥናቱ ውስጥ በዳውሮኛ ቋንቋ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቃላት ከነፍቺያቸው፤……..v

ጥናቱ የተካሄደበት ማህበረሰብ አካባቢያዊ ዳራ……………….……………..viii

ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ…………………………………………………1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................................................2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............................................................7

1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ..............................................................8

1.4. የጥናቱ ዓላማ.........................................................................8

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ.....................................................................9

1.6. የጥናቱ ወሰን ........................................................................9

1.7. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች.........................................9

1.7.1. ያጋጠሙ ችግሮች…….……………………………………………9

1.7.2. የተወሰዱ መፍትሔዎች……………………………………….……10

ምዕራፍ ሁለት፤ የክለሳ ድርሳናት………………………………………11

2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት....................................................................11

2.1.1. የ"Tookki Be'a" ቅኝት………………………………………………11

2.1.2. የሥርዓተ ከበራ (Ritual) ምንነት……………………………………11

2.1.3. የዘመን አቆጣጠር ዳራ………………………………………………13

2.1.4. የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት……………………………………………14

2.1.5. የአዲስ ዓመት ዋዜማ………………………………………………..17

2.2. የቀን አቆጣጠር በተለያዩ ሀገሮች......................................................17

2.2.1. የዘመን አቆጣጠር ሚቶሎጂያዊ ዳራ………………………………...18

2.2.2. የጥንት ግብጽ ዘመን አቆጣጠር……………………………………...18

2.2.3. የጁሊያን ካላንደር……………………………………………..………19

2.2.4. ግርጎሪያን ካላንደር……………………………………………………20

2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ...........................................................21

ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ዘዴና አካሄድ…………………………………….24

2.1. የጥናቱ ንድፍ............................................................................24

2.2. የመረጃ ምንጮች ........................................................................................24
2.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች .................................................................................25
2.3.1. የጥናቱ ቦታ ናሙና አመራረጥ.............................................25
2.3.2. የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ......................................25
2.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..............................................................................25
2.5. የመረጃ አደረጃጀት ........................................................................................28
2.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ....................................................................................28
ምዕራፍ አራት፤ መረጃ ትንተና...........................................................29
2.1. የመረጃ ትንተና ..........................................................................................29
2.1.1. የዳውሮ ብሔር (Tokki Be'aa) ዘመን መለወጫ ትርጉም............29
2.1.2. ቶክ-ቤኣ በዓል መቼ ይከበራል?...........................................32
2.1.3. የቶክ-ቤኣ በዓል ቅድመ ዝግጅቶች..........................................35
2.1.4. ለ"Tookki Be'a" በዓል የህብረተሰብ እና የቤተሰብ አባላት ድርሻ.....37
2.1.5. ለቶክ-ቤኣ በዓል የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች.................38
2.1.6. የቶክ-ቤኣ በዓል ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ..............................44
2.1.7. በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት የሚከወኑ ትዕምርታዊ ክዋኔዎች ትርጉም....48
2.2. የዳውሮ ማህበረሰብ ለቶክ-ቤኣ በዓል ያለው አመለካከት ..........................50
ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያ፣ ግኝትና አስተያየት........................................53
5.1. የጥናቱ ማጠቃለያ .......................................................................................53
5.2. የጥናቱ ግኝት ...........................................................................................54
5.3. አስተያየት ...............................................................................................55
ዋቢ ጽሑፎች.........................................................................57
አባሪዎች...............................................................................60

## በጥናቱ ውስጥ በዳውሮኛ ቋንቋ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቃላት ከነፍቺያቸው፤

Adilliya woy Ofintsaa - ጸደይ

Agenatta doyssaaddu - ጨረቃ ሙሉ ሆና ታየች

Agenatta lap'addu - ጨረቃ በከፊል ቀላች

Agenatta s'eeraaddu- ጨረቃ ወጣች

Aginatta miya kac'iyan beettaaddu - ጨረቃ በከብት ቀንድ ታየች

Assuuraa - በልግ

Awa doshuwa - ከሰዓት

Awa kawutuwa - ቀትር

Awa wulaa - ጸሐይ ግባት

Balgguwa - ክረምት

Bilahiya - ሌሊት

Boniya - በጋ

Bulliya - ከጎመን፣ ከቅቤ እና ከቅመማ ቅመም የሚዘጋጅ ባህላዊ ምግብ

C'ad'd'iya - የጎደሬ ቅጥቅጥ

C'eggennaa - በወራት ውስጥ መጥፎ የሚባሉ ቀናት

Dagaa - በአንድ መጠጫ ለሁለት ሆነው መጠጣት

Dawuro payduwa wogaa - የዳውሮ አቆጣጠር ስርዓት

Dubbusha - ትልቅ ጥላ ስር

Gallassaa - ረፋድ

Guurraa - ንጋት

Hamiliya - ሐምሌ

Hekka bilahiya - እኩለ ሌሊት

Hidaariya - ህዳር

Hinggic'c'aa - እንቁጣጣሽ

Hosppuniya - ሚያዚያ

Ichecheshiya - ጥር

K'aak'umiya - ጳጉሜ

K'ammaa - ማታ

Keeruwa - ቀጠሮ

Laappuniya - መጋቢት

Laytsa laamiya - ዘመን መለወጫ

Mask'k'alaa - መስከረም

Miyaata - ሚዜ

Naasiya - ነሐሴ

Omarssaa - ማምሻ

Salkketsaa - የእሸት በቆሎ ቂጣ

Shaata - ወጪት

Shambbaa - ለሁለት የተሰነጠቀ ቅል

Sid'id'uwa - ከጤፍ የሚዘጋጅ ባህላዊ መጠጥ

Siilissuwa - ከአይብና ከቅቤ ከተለያዩ ቅመማቅመሞች ጋር የሚዘጋጅ የዳውሮ ባህላዊ ምግብ

S'ik'inttiya - ጥቅምት

Tammiya - ሰኔ

Tanc'c'uwa - የጎመን ቅቅል ተከትፎ ከአይብ ከቅቤና ከቅመማ ቅመም ጋር ተዋህዶ የሚዘጋጅ የዳውሮ ባህላዊ ምግብ

Taysaasiya - ታህሳስ

Udduppuniya - ግንቦት

Ukitsaa - ቂጣ

Usuppuniy - የካቲት

Wonttaa - ጥዋት

Wonttumaatsaa - ሊነጋጋ ሲል

Wosolluwa - እንሶስላ

Wulaha - ምዕራብ

## ጥናቱ የተካሄደበት ማህበረሰብ አካባቢያዊ ዳራ

ይህ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት በዳውሮ ዞን ነው:: የዳውሮ ዞን በአሁኑ ሰዓት በአስር ወረዳዎችና በሁለት የከተማ አስተዳደር ተዋቅሮ ያለ ሲሆን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ከሚገኙ ዞኖች አንዱ ነው::


ዞኑ በሰሜን ኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን፣ በደቡብ ጋሞ ጎፋ ዞን፣ በምዕራብ ኮንታ ዞን እንዲሁም በምስራቅ ወላይታ ዞን እና በሰሜን ምስራቅ ካምባታ ጠምባሮ ዞኖች የሚያዋስኑት ነው::

የዞኑን አየር ንብረት ስንመለከት 25% የሚሆኑ ደጋ (በዚህ ስር የሚጠቃለሉ ወረዳዎች ቶጫ፣ማሪ ማንሳ፣ ከፊል ማረቃ እና ከጪ)፣ 45% የሚሆኑ ወይና ደጋ (በዚህ ስር የሚጠቃለሉ ወረዳዎች ኢሰራ፣ሎማ በከፊል፣ከፊል ማረቃ እና ገና ወልዲሃኔ ) ፣30% የሚሆኑ ቆላ (በዚህ ስር ታርጫ ዙሪያ ወረዳ፣ታርጫ ከተማ አስተዳደር፣ዛባ ጋዞ ወረዳ እና ዲሳ ወረዳዎች) የሚሸፍን ሲሆን ለእስትንፋስ ሙዚቃ መሳሪያው ስራ የሚውሉ እንጨቶች በአብዛኛው የሚገኙት ከቶጫ እና ከጪ ወረዳዎቸ ነው:: የዞኑ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህል፣ታሪክና እሴት እንዲሁም የአለባበስ ስርዓት አለው:: ባህሎችና ባህላዊ እሴቶች የሚያስደስቱና የሚያኮሩ የማንነታቸው መገለጫዎች ሲሆኑ ጊዜና ዘመናት ሲያልፉ ቀደምት አባቶች የሰሩትና ታሪክ ጥለው ያለፉት ድንቃድንቅ ባህልና ቅርፃቅርፆች እንዲሁም የተለያዩ ባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት ዛሬም ድረስ ዓለምን የሚያስደምሙ ሀብቶች እየሆኑ ይገኛሉ:: (ዎንታ 2003)

የዳውሮ ብሄረሰብ በጥቅሉ በሶስት ጎሳዎች የሚመደብ ሲሆን እነሱም" ማላ"፣"ዶጋላ" እና" አማራ" በመባል የሚታወቁ ናቸው:: እያንዳንዳቸው ስር የተለያዩ ጎሳዎች እንዳሉ የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ይገልፃል:: በተጨማሪም በማህበረሰቡ ውስጥ የማና ጎሳዎች (ሸክላ ሰሪዎች)፣ የማንጃ ጎሳዎች፣ ቆዳ ፋቂዎች እና የብረታብረት ቀጥቃጮች ይገኙበታል:: ብሄረሰቡ በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚጠቀመው ቋንቋ ዳውሮኛ ሲሆን በወላይታ አዋሳኝ ያሉት በከፊል ወላይተኛን፣ በኮንታ አዋሳኝ ያሉት በከፊል ኮንተኛን፣ በኦሮሚያ አዋሳኝ ያሉት በከፊል ኦሮምኛን፣ በካንባታ አዋሳኝ ያሉት ከፊል ካምባተኛን፣ በጋሞ ጎፋ አዋሳኝ ያሉት ከፊል ጋሞኛን ቋንቋዎች ይጋሩታል:: የቀደምት አባቶችን ጥበብ የሚዘክርና በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን

የተገነባው ብሄረሰቡን ከጠላት እንዲከላከል የተሰራው የንጉስ ሀላላ የድንጋይ ካብ እና የአንጋላት ጋቤ የፍርድ መደብ (ኢንዳ) ማህበረሰቡን ከሚያስተዋውቁት ቅርሶች የሚጠቀሱ ናቸው። (ጳዲቊ 2007)

የዞኑ ዋና ከተማ ታርጫ ከአዲስ አበባ 445 ኪሎ ሜትር በስተደቡብ ምዕራብ፣ ከሀዋሳ ከተማ 275 ኪሎ ሜትር፣ ከጅማ 140 ኪሎ ሜትር እንዲሁም ከወላይታ ሶዶ 180 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል።




ምስል አንድ፡- ጥናቱ የተካሄደበት ዳውሮ ዞን አስተዳደራዊ ካርታ (ምንጭ፡- ጳዲቁ 2007፤የዳውሮ ብሄረሰብ ታሪክና ባህል

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

የፎክሎር ጥናት ዘርፍ ውስጥ በርካታ ባህላዊ ሥርዓቶችና እሴቶች ይጠናሉ፡፡ ከነዚህም ባህላዊ ሥርዓቶች እና እሴቶች መካከል አንዱ የዳውሮ ብሔረሰብ የ Tokki-Be'aa (ቶክ-ቤኣ) ወይም ዘመን መለወጫ በዓል ክወና ሥርዓት ነው፡፡ የቶክ-ቤዓ በዓል ክወና ሥርዓት በማጥናት የማህበረሰቡን አኗኗር፣ ባህል፣ ማንነት፣ አስተሳሰብ እና የህይወት ፍልስፍና የሚጠቀሙ ጉዳዮችን ማግኘት ይችላሉ፡፡ ይህ ጥናት የሚያተኩረው በዳውሮ ብሔረሰቦች የ Tokki-Be'aa (ቶክ-ቤኣ) ወይም ዘመን መለወጫ በዓል ክወና ስርዓት ትንተና ነው፡፡

Kotack (2010) ባህል ከአንድ ማህበረሰብ በየጊዘዉ የምናደርገዉ እንቅስቃሴ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ በማህበረሰብ የሚከዉን ቁሳቁሶችና በማህበራዊ መስተጋብሮች መገለጫ ባህርያት ናቸዉ፡፡ ባህል ማለት ማህበረሰቦች በጋራ ያዳበሩትን የዕዉቀት ክምችት አስተሳሰብ ልማዳዊ ባህርያት ስሆን ከትዉልድ ትዉልድ የሚተላለፍ ነዉ፡፡ ባህል የሚለዉ ጽንስ ሀሳብ በባህረዉ ሰፍና ሁሉን አቀፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዘዉ በ1982 በሜክሲኮ ከተማ በዩኒስኮ አማካይኝነት በተካሄደዉ ጉባኤ በተደረሰበት ስምምነት መሰረት ባህል የሰዉ ልጅ ሰብዓዊና ምክንያታዊ ፍጡር እንድሆን ያስቻሉ ወይም ከለሎች ፍጡርን ለመለየት የበቃን ማንኛቸዉም ምሁራን ስነ ምግባራዊ አካላዊ ቴክኒካናዊና እዉቀት የራስን የማሰለጠን ሁኔታዎች የሚያጠቃልል ጽንስ ሃሳብ ነዉ፡፡

ይህ ጥናት በ Tokki-Be'aa (ዘመን መለወጫ) በዓል አከባበር ከሌሎች ክብር በዓላት በምን እንደሚለይና አጠቃላይ ለበዓሉ አከባበር መሰረት ያደረገ ክዋናዎች ለብሔረሰቡ የሚሰጥ ፋይዳና ለበዓሉ አከባበር ምክንያት የሚሆኑትን ጉዳዮችን ያካተተ ጥናት ነዉ፡፡

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተደራጀ ሲሆን ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አብይና ንዑሳን ዓላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን ተካትቶበታል፡፡
ምዕራፍ ሁለት የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች፣ ንድፈ ሀሳቦችና ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የተዳሰሰበት ክፍል ነው፡፡ ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ንድፍ፣ የመረጃ ምንጮች፣ የናሙና

አመራረጥ ዘዴዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ መተንተን ዘዴዎችና የጥናቱ ስልት አካትቷል፡፡

ምዕራፍ አራት የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ የቀረበበት ክፍል ሲሆን ምዕራፍ አምስት የጥናቱ ማጠቃለያ፣ ግኝት እና አስተያየት ቀርቦበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋሉ የተለያዩ ዋቢ ጽሑፎች እና የተለያዩ አባሪዎችም በጥናቱ መጨረሻ ክፍል ቀርበዋል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ በጋራ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ የህይወት ዘመኑን ጉዞ ለኑሮ ምቹ ለማድረግ እና የተቀላጠፈ ህይወት ለመኖር የተለያዩ ስልቶችን ሲጠቀም እንደኖረ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በጥንት ጊዜ ሰዎች የዕለት ተለት ሥራቸውን ለማከናወንና የተከናወኑትን ለማወቅ እንዲመቻቸው ጊዜን፣ ሰዓታትን፣ ቀናትን፣ ሳምንታትን፣ በወራትና በዓመት የሚከፋፍሉበት ሂደት የዘመን አቆጣጠር ስልት ይባላል፡፡ አርሶ አደሮች በድሮ ጊዜ መቼ ማረስና መዝራት እንደሚገባቸው የጊዜ አቆጣጠር ስልት ካለመኖራቸው የተነሳ ሲቸገሩ እንደነበር ጥናቶች ይጠቁማሉ (ማሞ 2007 ዓ.ም ገጽ 2)፡፡

እኚሁ ምሁር አክለውም "የዘር፣ የአጫዳ፣ የአረም፣ ወቅት አዘጋጅተው ቢጠቀሙም ከወቅቶች መፈራረቅ ጋር የሚጣጣም የዘመን አቆጣጠር ስልት ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ ይህን ለማወቅ ግማሾቹ በጨረቃ፣ ግማሾቹ በፀሐይ፣ ሌሎቹ ደግሞ በፀሐይ እና በጨረቃ በጣምራ ስልት መቁጠር ጀመሩ፤ በጨረቃ ለሚያምኑት ሰዎች አንድ ወር ማለት ከአንድ ሙሉ ጨረቃ እስከሚቀጥለው ሙሉ ጨረቃ ድረስ ይዘልቃል፡፡" ሲሉ ይልጻሉ፡፡

> አስፋው (2013) የዘመን አቆጣጠር ማለት ዕለታትን፣ ሳምንታትን፣ ወራትን፣ ወቅቶችን እና ዘመናትን በፀሐይ፣ በጨረቃ እና በከዋክብት ዙር እየመጠኑ፤ ምድር ላይ በሚታዩት ተፈጥሮአዊ ጠባያት ጋር በማስተባበር ወጥ የሆነ የምልልስ ጊዜያቸዉን ለይቶና ለክቶ በቁጥር የማሳወቂያ ሥርዓት ነዉ፡፡ ይህንንም ዘዴ በመጠቀም መቁጠር የተጀመረዉ ከአዳም ጀምሮ መሆኑን እና የአዳም ሰባተኛ ትዉልድ የሆነዉ፣ መምህር ሄኖክ የተባለ ነብይ እንደነበረና የባፈዉም ቀመር እንዳለ ሃያማኖታዊ ማስረጃዎች የሚቀርቡ ቢሆንም፤

ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እዉነትነቱ ሊረጋገጥና ዕዉቅና ሊያገኝ አልቻለም። ይሁን እንጂ፤ የሰዉ ልጅ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ የተነሳ ተራርቆ ቢገኝም፤ እነዚህን ብርሃናዊ የሰማይ አካላት ለዘመን አቆጣጠር ዘዴዉ በመሠረታዊያንነት ሲገለገልባቸዉ እንደቆየ የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ አለ። በዋናነት የአቆጣጠሩ መነሻ ያደረጋቸዉ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ እና ከዋክብት በየተራ እየወጡና እየገቡ ለዘለዓለም ዓለምን እንደሚዞሩ በመገንዘብ በምልክትነት የተገለገለባቸዉና እየተገለገለባቸዉ መሆኑ ነዉ። ይህ አስተሳሰብ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረና በዉስጡ የተለያዩ አስተሳሰቦች እየተለወጡ የመጡበት ነዉ። ለዚህ መገለጫ የሚሆነዉ፤ የጥንት ሰዎች መሬት በአንድ ስፍራ ላይ የቆመች መሆኗን እና እነዚህ ሰማያዊ አካላት ዙሪያዋን እንደሚዞሩ ማመናቸዉ ሲሆን፤ የስነፈለግ ተመራማሪዉ ኒኮላስ ኮፐር ኒክስ አዲስ ሃሳብ ይዞ እስከ ተነሳበት ዘመን የዘለቀ ነባር አስተሳሰነብ ነዉ። በማለት በጥናታቸው አብራርተዋል።

አስፋው (2013) አክለውም ኒኮሊስ ኮፐርኒክስ የኖረዉ እንደ አዉሮፓዊያን አቆጣጠር ከ1473-1543 ሲሆን፤ ይዞት የመጣዉ አዲስ ሳይንሳዊ ሀሳብ የቀድሞዉን የሰዉ ልጆች ሀሳብ የሚሽር ነበር። በአንድ ስፍራ ላይ ረግታ የቆመችዉ መሬት ሳትሆን፤ መሬት ራስዋ ፀሐይን ከሚዞሩ ሰማያዊ አካላት አንዷ መሆኗን እና ፀሐይን የምትዞርበት የጊዜ ርዝመትም ሊለካ የሚችል እንደሆነም ዓለምን አሳመነ። በዚሁ መልክ ጨረቃ መሬትን የምትዞረዉ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሆነና የሷም የዙር እንቅስቃሴ ሊለካ እንደሚችል አረጋገጠ።

ይህ በሳይንስ ተረጋግጦ በሥርኣተ ትምህርት ዉስጥ ትዉልድ ሁሉ ተምሮ የየራሱን ተተኪ እየዞረች መሆኑ እየተነገረ ነዉ። በሰከንድ 220 ማይልስ እየተወነጨፈች የፍኖተ ሀሊብን ዙር 220 ዓመት እንደምትጨርስ ተጽፎ ተተርጉሟል።

የዘመን አቆጣጠር ታሪኮችን ስንዳስስ የምናገኘዉ እዉነታ፤ የሰዉ ልጅ ግምታዊ የጊዜ መጠን ሳያረካዉ በመቅረቱ፤ መቼ ማረስ፤ መቼ መዝራትና መቼ ሰብሉን መሰብሰብ እንደሚገባዉ፤ በየትኛዉ ጊዜ መስራትና በየትኛዉ ጊዜ መፀለይ እንዳለበት የሚያሳዉቀዉ፣ የተጻፈ ወይም ቋሚ የሆነ የጊዜ

ሰሌዳ ያለዉ የዘመን አቆጣጠር ዘዴ መመሥረት መጀመሩን ነዉ፡፡ በዚህም የተነሳ እነዚህን ብርሃናዊ የሰማይ አካላት መሠረት በማድረግ፤ ጊዜን በሰዓታት፣ በዕለታት፣ በወራት እና በዘመናት እየለካ የመቁጠር ተመሳሳይ ዕሴት ሊያዳብር ቢችልም፤ በባህልና በመልክዓ ምድራዊ ክልል ልዩነትና መራራቅ የተነሳ፤ የተለያዩ የዘመን አቆጣጠር አይነቶች ባለቤት መሆን እንደቻለ በታሪኩ አንፃር ማየት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ የአቆጣጠር ዓይነቶች በዋናነት የሚታወቁት የፀሐይ (solar) አቆጣጠር፣ የጨረቃ (Lunar) አቆጣጠር፣ የፀሐይና የጨረቃ ጥምር አቆጣጠር (Luni-solar) እና የአዉደ ከዋክብት (Sidereal) አቆጣጠር ሲሆኑ፤ በተጓዳኝ የዕፅዋትን እና የዛፍችን፣ የእንስሳትን እና የነፍሳትን ተጥሮአዊ ሁኔታዎች ማመሳከርንም ይጨምራል፡፡ ዕፅዋቱ እና ዛፎቹ፣ መቼ እንደሚበቅሉ፤ መቼ እንደሚያብቡ፤መቼ እንደሚያፈሩ፤ ፍሬያቸዉም መቼ እንደሚጎመሩ ወይም እንደሚደርስ እና መቼ ቅጠላቸዉ እንደሚረግፍ ወይም እንደሚደርቁ ማገናዘብን የሚጠይቅ ሲሆን፤ እንስሳቱንና ነፍሳቱንም በሚመለከትም የመራቢያ ጊዜያቸዉን፣ ከቦታ ወደ ቦታ የሚያደርጉትን የጋራ እንቅስቃሴ በመከታተል እና ምልከታ በማድረግ የወቅቶችን ዘር በትክክል የማወቂያ ዘዴዎችንም የሚያጠቃልል ነዉ፡፡

የጨረቃ አቆጣጠር (Lunar Calendar)፡- አዲስ የተወለደችን ጨረቃ መሠረት አድርጎ የመቁጠር ዘዴ ነዉ፡፡ አንድን ወር በ29 ሰዓት ከ12 ሰዓት በማስላት አንድን ዓመት በ354 ቀን ይለኩበታል፡፡ ይሁን እንጂ፤ ከፀሐይ አቆጣጠር በ11ቀን ከ6 ሠዓት ያነሰ በመሆኑ ወቅቶችን በትክክል ለመለየት ያስቸግር ነበር፡፡ አገልግሎት ላይ ዉል የነበረባቸዉ ህዝቦችና ሀገራት ጥንታዊ እስራኤላዊያን፣ ሮማዊያን፣ ሴልተሶች እና ጀርመናዊያን ሲሆኑ፤ በአሁኑ ጊዜ ያለዉን የእስልምና ሃይማኖታዊ አቆጣጠር የሚመስል እንደ ነበር ተመዛግቧል፡፡

"In the past, the first sighting of the young waxing crescent Moon just after sunset marked the start of each month. Today, tables predicting the first appearance of the crescent Moon are often used instead. Lunar calendars were

developed by the ancient Hebrews, Romans, Celts and Germans. The Islamic calendar is the major lunar calendar in use today." Alan Longstaff, (2005).

በሌላ በኩል በዓለም የካሌንደር ታሪክ ዉስጥ ጥንታዊ ሱሜራዊያን ለመጀመሪያ ጊዜ የጨረቃን አቆጣጠር የመሰረቱ መሆናቸዉ ተተርኮ እናገኛለን፡፡

"The ancient Sumerians devised the first Lunnar Calender about 5,000 Years ago. Later, Babilonians divided months in to weeks and a week in to 7 days." አስፋው (2013) Everett Fisher. (p.387)ን በመጥቀስ፤

የዚህ ጥናት ትኩረት ጨረቃን (Lunar) አቆጣጠር መሠረት አድርጎ በአሮጌ ዓመት ማብቂያ እና በአዲስ ዓመት መባቻ የሚከበረውን የዳውሮን ብሔረሰብ አዲስ ዓመት (ቶክ-ቤኣ) የሚመለከት ሲሆን የዳውሮ ብሔረሰብ የስራ ጊዜያቸውን፣ የእርሻና የአጨዳ ወቅታቸውን በዚህ አቆጣጠር ተንተርሰው የሚያደርጉ ስለሆነ ከዚህ ሀሳብ ጋር እየተነጻጸረ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

ዩኒክ ኢትዮጵያ (2008) በዓለማችን፣ በአህጉራችን እና በሀገራችን የሚኖረው ማህበረሰብ በየክፍለ ዘመናቱና በየጊዜያቱ ከስልጣኔ ማማ ላይ የተንሰራፋበት የራሱ ጊዜ አለው፡፡ በዚህም የተለያዩ ክዋኔዎችን በማበርከት የስኬትን ቁንጮ ለመቆናጠጥ ተችሏል፡፡ ከዘመን ዘመን፣ ከትውልድ ትውልድ መሸጋገር የሚችሉ ምጡቅ ግኝቶች አሁንም ላለው ማህበረሰብ የመንደርደሪያ ግኝት በመሆን በማገልገል ላይ ያሉ የተለያዩ አበይት ጉዳዮች አሉ፡፡ የዚህ ሁሉ መሠረቱ ደግሞ ሁለንተናዊ የሆነ የስልጣኔ ባለቤት መሆን ነው፡፡

ከስልጣኔ ትርጓሜም የምንረዳው አንድ ህዝብ ወይም መንግስት ባሳለፈበት ዘመን ትቶት የሚያልፈው ታሪካዊ፣ ባህላዊና ትውፊታዊ እሴቶች እንዳሉት ነው፡፡ ከእነዚህ እሴቶች መካከል ደግሞ የዘመን አቆጣጠር ቀመር ዋነኛው ነው፡፡

ይህም ጥናት ደግሞ በጨረቃ መውጣት ላይ መሠረት ተደርጎ የሚከበረውን የዳውሮ ብሔረሰብ ቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል ክወና ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የበዓሉ አከባበር በጨረቃ መውጣት እንዴት እንደሚገለጽ የሚተነትን ይሆናል፡፡

Staff (2016) በተለያዩ ሀገራት ስለሚከበር አዲስ ዓመት የሚከተለውን ይላሉ፡፡ "ብዙን ጊዜ የአዲስ ዓመት በዓላት በመላው ዓለም ሲከበሩ ለመጪው አመት

መልካም እድል ለማምጣት አላማ ያላቸውን ወጎች ያካትታሉ፡፡ ብዙ አገሮች በአዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ቀን በተለያዩ ዝግጅቶች ለማክበር ይመርጣሉ:: በተለይ በአዲስ ዓመት ዋዜማ ርችቶችን መጠቀም የተለመደ ሲሆን መጥፎ ነገሮችን በእሳት እና በታላቅ ጩኸት ለመከላከል መጀመሪያ ጥቅም ላይ እንደሚውል ይታሰባል፡፡ ብዙ የአውሮፓ ሀገራት የአሮጌ አመት መጨረሻ ቀንን እንደ ይፋዊ አዲስ አመት ይቆጥራሉ፡፡ ምንም እንኳን አዲስ ዓመት መባቻውን የጋራ ቀን አድርገው ቢጋሩም በአለም ዙሪያ ያሉ ሀገሮች አዲሱን አመት በበርካታ መንገዶች ያከብራሉ፡፡ የዘመን መለወጫ በዓላትን የሚያሳዩ የተለያዩ ምግቦች እና ወጎች አዲስ አመት ከሚገባበት ወቅት ጋር እንደሚያደርጉት ከብሔረሰቡ ባህል ጋር ተመሳሳይነት አላቸው:: ለምሳሌ:- የአውስትራሊያ የአዲስ ዓመት ዋዜማ ግብዣዎች ብዙውን ጊዜ በባህር ዳርቻ ላይ  ይካሄዳሉ:: የአዲስ ዓመት ዋዜማ ክብረ በዓላት የሚከናወኑት ሰዎች ብርድ ባለበት ቀዝቃዛ የውጪ ሥነ ሥርዓቶች ላይ ነው፡፡

በጃፓን አዲሱ ዓመት በዓመቱ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት በዓላት አንዱ ነው፡፡ የጃፓን አዲስ ዓመት ከአዲስ ጅምር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ቤተሰቦች ከዚህ በፊት ያጋጠሙትን ችግሮች ለመሰናበት (ዓመቱን የሚረሱበትን) ድግሶችን ያካሂዳሉ፡፡ ቤቱን ከላይ እስከ ታች ማጽዳት የጃፓን ቤተሰቦች ለአዲሱ ዓመት የሚያዘጋጅ አስፈላጊ ሥነ ሥርዓት ነው፡፡ ልዩ በዓላት በቤተእምነቶችም ውስጥ ይካሄዳሉ፡፡ የጃፓን ሰዎች አዲስ ዓመት መድረሱን ለማረጋገጥ ለጓደኞቻቸው እና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው ልዩ የአዲስ ዓመት ካርዶችን ይልካሉ:: የቤተሰብ አባላት ባሳለፉት ዓመት ስለለገጠማቸው መጥፎ እድላቸው አጭር ማስታወሻ ጽፈው ወረቀቶቹን በቤት ውስጥ በተሰራ ገለባ ውስጥ ያስቀምጧቸዋል፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያም ከጥንት ከአክሱም ዘመነ መንግስት በፊት ጀምሮ የራሷ የሆነ የቀን አቆጣጠር እንዳላት ጥናቶች ያመላክታሉ (ስርገ ሀብለስላሴ፣ 1972 ዓ.ም፤ ዋለልኝ እምሩ 2000 ዓ.ም)፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የየራሳቸው የሆነ ዘመን መለወጫ ሲኖራቸው ዕለቱን ወይንም ሳምንቱን በተለያዩ ክዋኔዎች ያከብሩታል::

የዳውሮ ብሄርም የራሱ የሆነ የዘመን መለወጫ በዓል እና የጊዜ መቁጠሪያ ጥበብ አለው፡፡ የዘመን መለወጫውም ቀን 'ቶክ በዓ' ይባላል፡፡ የቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል በዚህ ቀን ወይም ጊዜ ተጀመረ የሚል ትክክለኛ መረጃ ባይታወቅም የጥንት

ዳዉሮዎች የጨረቃን መዉጣትና መጥለቅ ተከትለዉ የሚቆጥሩት የዘመን ቀመር እንደሆነ በአሮጌዉ ዓመት የመጨረሻ ዕለት፤ በአዲሱ ዓመት ዋዜማ ምሽት የዘመን መለወጫ በዓላቸዉን የሚያከብሩት ክብረ-በዓል ሲሆን፤ ከአዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ለአንድ ሳምንት ጎረቤት፣ ወዳጅ፣ ዘመድ በጋራ የሚያከብሩት ነዉ።

የዳውሮ ብሔር ቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓልን ለማክበር የራሱ የሆነ የቀን አቆጣጠርና የጊዜ ቀመሮችን ይጠቀማል። የተለያዩ ቀመር ሲጠቀሙ የተለያዩ ምልክቶችን በመጠቀም የሰዓታቶች ልዩነት፣ የአንድ ቀንን በማታና በቀን በማከፋፈል፣ የቀናትን፣ የሳምንታትን፣ የወራት አቆጣጠርን እና የወቅቶች አቆጣጠርን በዳውሮ ከተለያዩ ክስተቶች ጋር አገናኝተው ይጠቀማሉ። መምሸትና መንጋትን፣ የዶሮና የወፍ ጨኸትን፣ የፀሐይ ጥላና ቃጠሎን፣ … ወዘተ መሠረት ያደረገ ነው።

ቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል በተለይ ጥንት አባቶች ጊዜን ለመለካት ገመድ እየቋጠሩ በአንድ ቀን ውስጥ የሚገኙ ሰዓታትን፣ ሳምንታትን፣ ወራትን እንዲሁም ዓመታትን በመለካት የዓመቱ መጨረሻ ቀን እና በአዲሱ ዓመት የመጀመሪያ ዕለት ለዚህ ያበቃቸዉን ፈጣሪ የሚያመሰግኑበት ቀን የቶክ- ቤዓ በዓል ማክበር የተጀመረበት ጊዜ እንደሆነ መረጃዎች ያስረዳሉ።

ይሁን እንጂ በዓሉን ማክበሩ ለማህበረሰቡ የሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ፋይደው በትክክል አልተጠናም (አድማሱ 2008፣130)።

የዚህ ጥናት ርዕስ ትኩረት የሆነው የዳውሮ ብሔረሰብ ቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል አከባበር ክወና ሥርዓትም በብሔሩ ዘንድ ሲከበር የተለያዩ ጉዳዮችን (በበዓሉ የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦችን፣ መጠጦችን፣ የአለባበስ ሥርዓቶችን፣ እርስ በርስ የመመራረቅ ሂደቶችን) አካትቶ የሚከወን ነው።

ስለሆነም የበዓሉን አከባበር ክወና ሥርዓት በጥናት ማስደገፍ አንዳች ውጤት ሊያስገኝ ይችላል ከሚል እምነት ይህ ጥናት በዳውሮ ብሔረሰብ ቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል ክወና ስርዓት ላይ የሚደረግ ይሆናል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አድማሱ (2008) የዳውሮ ብሔረሰብ ቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል ለማህበረሰቡ ያለው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው የጎላ ቢሆንም ተገቢ ትኩረት እንዳላገኘና በጥናት እንዳልተደገፈ ይገልጻሉ።

በመሆኑም የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የበዓሉ ክወና ስርዓትን በጥናት ማስደገፍ አስፈላጊ በመሆኑና የቶክ ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓልን የዳውሮ ብሔረሰብ ለምን እንደሚያከብሩና እንዲያከብሩት የሚያደርገው ምክንያት ምን እንደሆነ ለመለየት ነው፡፡ በዳውሮ ብሔረሰብ የቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል በገጠርም ሆነ በከተማ ላይ ሰዎች ለማክበር ያላቸው ናፍቆት እና ደስታ ወደር የለውም፡፡ ስለዚህ አጥኚው ጉጉታቸው ከምን የተነሳ እንደሆነ በጥናት አስደግፎ ለማወቅ ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ በዚህ ርዕስ ለማጥናት ተነሳስቷል፡፡

በተጨማሪም አጥኚው የብሔሩ ተወላጅ በመሆኑ የዚህን ባህላዊ ቅርስ አከባበር በተለያዩ አጋጣሚዎች የመሳተፍ እድል ነበረውና፤ በመሆኑም ከበዓሉ ጋር በጋራ የሚከወኑ በርካታ ባህላዊ ትዕምርቶችን ሲመለከት ክንዋኔያቸው ተመልካችን ከማስደመም በላይ አይቀሬነታቸው ለምን ይሆን የሚለውን በጥናት አስደግፎ ለማረጋገጥ ካለው መሻት አጥኚው በዚህ ርዕስ ለማጥናት ተነሳስቷል፡፡

## 1.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ጥናቱ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ✓ የ "Tookki Be'a" (ዘመን መለወጫ) በዓል ለብሔረሰቡ ያለው ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ ምንድነው?
- ✓ በበዓሉ ወቅት የሚደረጉ የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎች ትርጉማቸው ምንድነው?
- ✓ በዓሉ በማህበረሰቡ ዘንድ ምን ዓይነት አመለካከት አለው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዳውሮ ብሔረሰብ ዘንድ የሚከበረውን የ"Tookki Be'a" (ዘመን መለወጫ) በዓል ክወና ሥርዓትን መተንተን ነው፡፡ የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የ"Tookki Be'a" (ዘመን መለወጫ) በዓል ለብሔረሰቡ ያለውን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ መተንተን፤
- በበዓሉ ወቅት የሚደረጉ የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎች ትርጉም መግለጽ፤
- ማህበረሰቡ ስለበዓሉ ምን ዓይነት አመለካከት እንዳለው ማብራራት የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቄሜታ

አንድ ጥናት ሲካሄድ ለተለያዩ አካላት ሊኖረው የሚችል ፋይዳ ታሳቢ በማድረግ ይካሄዳል፡፡ በተለይ ባህላዊ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ሲነሱ የዚያን ማህበረሰብ ወግና ስርዓት ተነጥሎ የማይታይ እንደመሆኑ መጠን ለማህበረሰቡ የሚኖረው ፋይዳ የጎላ ይሆናል፡፡

ይህም ጥናት ይኖሩታል ተብሎ የሚጠበቁ ጠቀሜታዎች በበቅድሚያ የቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል አከባበርን ቀጣይ ትውልድ እንዲረዳው በሰነድ ቅርስነት ለማስቀመጥ ሊጠቅም ይችላል፡፡

በመጨረሻም በዚህ ርዕስ ለሚያጠኑ አጥኚዎች እንደነሻ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ወሰን በዳውሮ ዞን የሚከበረው የዘመን መለወጫ በዓል ቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በመሆኑም በዞን ውስጥ ሁሉም አካባቢዎች በዓሉ የሚከበርባቸው ቢሆንም ለአጥኚው ካለው ጊዜና ገንዘብ አቅም የተነሳ በጥናቱ የተሳተፉት ገና ወረዳ እና ታርጫ ከተማ አስተዳደር ናቸው፡፡

ከይዘት አንጻር ጥናቱ በአብዛኛው ጊዜ የጨረቃ አቆጣጠርን መሠረት ያደረገው የብሔረሰቡን ዘመን መለወጫ በዓል ቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) ብቻ ላይ መሠረት በማድረግ ተካህዷል፡፡ ዳውሮ የሚያከብራቸው ሌሎች በርካታ በዓላት ቢኖሩትም አጥኚው ካለው ጊዜ፣ የኢኮኖሚ አቅም ውስንነትና በዓላቱ ካላቸው ማህበራዊና ባህላዊ መዳረሻ ስፋት መነሻ በ"Tookki Be'a" (ዘመን መለወጫ) በዓል ክወና ሥርዓት ላይ ብቻ በማተኮር ጥናቱን አካሂዷል፡፡

## 1.7. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

### 1.7.1. ያጋጠሙ ችግሮች

በዚህ ጥናት በሌሎች የመስክ ጥናቶች የሚጠበቁ የመጓጓዣ፣ የኢኮኖሚ ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ በፊት ከጥናት ርዕሱ ጋር በተገናኘ በስፋት የተሠሩ የጥናት ሥራዎች ያለመገኘታቸው ለመረጃ ሥራ በጣም አዳጋች ነበር፡፡

የጥናቱ መረጃ የሚሰበሰብበትና በዓሉ የሚከበርበት ወቅት የተለያየ በመሆኑ ከእውነተኛ የመስክ ምልከታ መረጃውን መሰብሰብ እና በኢ-ተፈጥዊ መቼት መረጃን

በምሰበሰብበት ጊዜ መረጃ ሰጪዎቹ እንደ ተፈጥሯዊ መቼት ሆኑ ያለመከወን በመረጃ ሥራ ወቅት ሌላው እንቅፋት ነበር፡፡
ለበዓሉ የሚዘጋጁ ሁሉንም ባህላዊ ምግቦች ለማዘጋጀት ብዙ በጀት የሚጠይቅ መሆኑም በጥናት ሥራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ናቸው፡፡

### 1.7.2. የተወሰዱ መፍትሔዎች

ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ከዚህ ርዕስ ጋር በተገናኘ የተደረገ ጥናታዊ ሥራ በስፋት ባይገኝም በጥቂቱ ከተገኙት ጥናቶች በተጨማሪ ከሌሎች ጽሑፎች በሰነድ ፍተሻና ታሪኩን ከሚያውቁ ሰዎች በቃለ መጠይቅ መረጃውን የመሰብሰብ ሥራ ተሰርቷል፡፡
ኢ-ተፈጥሯዊ መቼትን በመጠቀም መረጃን የመሰብሰብ ሥራ ተሰርቷል፡፡
ለበዓሉ የሚዘጋጁ ሁሉንም ባህላዊ ምግቦች ማዘጋጀት ብዙ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ የሚቻሉትን በማዘጋጀት ያልተቻሉትን ደግሞ አሠራራቸውን በመተንተን ማቅረብ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ የክለሳ ድርሳናት

ይህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ድርሳናት የሚቀርቡበት ክፍል እንደመሆኑ የስርዓት ምንነት፣ የዘመን አቆጣጠር ዳራ፣የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት፣ የአዲስ ዓመት ዋዜማ፣ የቀን አቆጣጠር በተለያዩ ሀገሮች፣የጥንት ግብጽ ዘመን አቆጣጠር፣ የጁሊያን ካላንደር፣ ግርጎሪያን ካላንደርና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የሚሉ ርዕሶች በዚህ ምዕራፍ ስር ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

## 2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1. የዘመን አቆጣጠር ቅኝት

ከሥልጣኔ ትርጉም የምንረዳው አንድ ህዝብ ወይም መንግሥት ባሳለፉበት ዘመን ትቶት የሚያልፈው ታሪካዊ፣ ባህላዊና ቁሬታዊ እሴቶች እንዳሉት ነው፡፡ ከእነዚህ እሴቶች መካከል ደግሞ የዘመን አቆጣጠር ቀመር ዋነኛው ነው፡፡ እንደ አጠቃላይ በሀገር ደረጃ ለሥልጣኔያችን ስኬት መነሻነት የምንጠቀመው ሀገራዊ የዘመን አቆጣጠር ቀመር ባለቤት ነን፡፡ ሆኖም ካሉን የተለያዩ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ስብስብ መነሻነትና እነኚህም ብሔር ብሄረሰቦች ካስመዘገቡበት የሥልጣኔ ስኬት ዕድገት በመነሳት የተለያዩ ባህላዊ የዘመን አቆጣጠር ቀመሮች በየብሔረሰቡ ይገኛሉ፡፡

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ዳውሮ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ ባህል፣ ወግ፣ ልማድና እሴት ባለቤቶች ናቸው ፡፡

መቼም ዋናው ርዕሰ ጉዳይ የብሔሩ ዘመን መለወጫ ክብረ በዓል ስለሆነው የ"Tookki Be'a" በዓል ቅኝታዊ ዳሰሳዎችን ማቅረብ ነው፡፡ ፎክሎር ብዙ ዘርፍ እና ቅርጽ አለው፤ በመሆኑም በባህል፣ በልማድና በወግ የሚሰሩትን፣ የሚናገሩትን፣ የሚለብሱትን፣ የሚበሉትንና የሚጠጡትን ቁምነገሮች እንደ ቅርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር ዘርፍ ነው፡፡

### 2.1.2. የሥርዓተ ከበራ (Ritual) ምንነት

ስለ ሥርዓት ምንነት የሚሰጡ ብያኔዎች በጣም በርካታና አሻሚነት የሚታይባቸው እንደሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ ሲሉ ለማ (2006) ይገልጻሉ፡፡ለማ (2006) Morris (1992)ን ጠቅሰው የሥርዓትን ምንነት ሁሉም እያወቀው አንድም ሰው ሊበይነው ከማይችላቸው ቃላት ውስጡ አንዱ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ (Ritual is one of those

words where we all know what it means but no one can define it.) ሲሉ ይገልጻሉ። በቃሉ አጠቃቀምና በክንዋኔዎቹ አረዳድ ዙሪያ ሰፊ ልዩነቶች መኖራቸውን ደግሞ Roth (1995)ን ዋቢ አድርገው ያስረዳሉ። በጽንሰ ሀሳቡ ምንነትና በክንዋኔዎቹ ዙሪያ ለሚታዩት ልዩነቶች የጽንሰ ሀሳቡ ሰፊ ክስተቶችን ለመመርመር መዋል፣ (ከሽግግር ሥርዓቶች እስከ ቡድናዊ የገጽ ለገጽ መስተጋብሮች የሚታዩ "ህግጋትና ደንቦች")፣ አስተዋጽኦ ሳያደርግ እንዳልቀረ Roth (1995) በተዘዋዋሪ መንገድ ይጠቁማሉ። ክብደት የሚሰጣቸውና የሚሸፍናቸው ሰፊ ጉዳዮች የሥርዓት ጽንሰ ሀሳብ እንዲዋዥቅ፣ እንዲሸራረፍና በሂደትም እንዲያፈነግጥ አድርገውታል።

የሆነ ሆኖ ግን ሥርዓት በድርጊት የተሞላና ማን ምን ማድረግ እንዳለበት በቡድናዊ ስምምነት በሚወሰን ዘልማዳዊ ደንብ የሚገዛ፣ ተደጋጋሚነትና ትዕምርታዊነት ያለው ቡድናዊ ክበራ በመሆኑ ዙሪያ ብዙ የዘርፉ ተመራማሪዎች ይስማማሉ በማለት ለማ (2006) ያስረዳሉ።

Myerhoff (1977)ን ዋቢ አድርገው Sims እና Stephens (2005፣95) እንደሚያስረዱት ሥርዓቶች በቅደም ተከተል የተደራጁና ዘውትር ትዕምርቶችን፣ ድርጊቶችን፣ ድግግሞሾችን ያካተቱና ምናልባትም ሥርዓቶች መሆናቸውን ለመገንዘብ የሚያስችሉ፣ መቼ እንደሚጀምሩና እንደሚጨርሱ የሚያመላክት ድንበር ያላቸው ክወናዎች ናቸው። ስለሥርዓት ምንነት ሲነሳ እንደነDurkheim (1912)፣ Turner (1967) እና ተከታዮቻቸው ከትዕምርታዊነቱ ይልቅ ተግባራዊነቱ ላይ ትኩረት የሚሰጡ ተመራማሪዎች እንዳሉ Marshall (2002)ን በመጥቀስ ለማ (2006፣24) ይገልጻሉ። "ማርሻል ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አብዛኞቹ ተመራማሪዎች ስለስርዓቶች ሲያስቡ ከትዕምርታዊ ይዘታቸው ላይ አትኩረው፣ ሥርዓት፣ ሀሳብ ትዕምርታዊ በሆነ መንገድ የሚገለጽበት፣ የሚተላለፍበትና የሚጠናከርበት አንድ ተጨማሪ መነገድ መሆኑን በማሳየት ላይ እንዳተኮሩ ጠቁመው እንዲህ ዓይነቱ አንጻር እንዚህ የተለዩ መልዕክቶች በእንዲህ ዓይነት የተለየ ሁኔታ ለምን እንደተገለጹ እንደማያብራሩ ያስረዳሉ።" በማለትም ሀሳባቸውን ያክላሉ።

Staal (1979፣4)ን ዋቢ አድርገው ለማ (2006) ሥርዓት በዋናነት ክንውን መሆኑንና ክንውኑም ግልጽ በሆኑ ደንቦች መገዛቱን ጠቁመው ጠቃሚው ጉዳይ

የሚደረገው ነገር እንጂ የሚታሰበው፣ የሚታመንበት ወይም የሚባለው እንዳልሆነ በመግለጽ የሌሎችን ሀሳብ ይጋራሉ፡፡

በSims እና Stephens (2005፣94) የቀረበው የሥርዓት ምንነት ገለጻ ከፍ ሲል ሥርዓትን ከክወናዊነቱ ወይም ከትዕምርታዊነቱ ላይ ብቻ በማተኮር ለመበየን የሞከሩትን ተመራማሪዎች ለማስታረቅ የሚሞክር ይመስላል፡፡ Sims እና Stephens ሥርዓት ለአንዳች ዓላማ ለምሳሌ ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ለሚደረግ ሽግግር ከመሠረታዊ የህይወት ምዕራፎች ወይም የቡድን ልምዶች መግባትን ወይም መውጣትን ለማስረገጥ የሚከወን እንደሆነ ያስገነዝባሉ ሲሉ ለማ (2006) እነዚህን ምሁራን በመጥቀስ ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች ለመረዳት እንደሚቻለው ሥርዓት በትዕምርቶች፣ በክንውኖች፣ በቅደም ተከተል በሚቀርቡ ድርጊቶች ተገንብተው በቡድን ዘልማዳዊ ደንብ እየተመሩ በተደጋጋሚ በሚከወኑ ልማዶች ላይ ለተመሰረቱ ለከዋኞቸው ቡድን አንዳች ማህበራዊ ፋይዳ ላላቸው ከበራዎች የሚሰጥ መጠሪያ እንደሆነ ለማ (2006፣25) ይገልጻሉ፡፡

### 2.1.3. የዘመን አቆጣጠር ዳራ

አስፋው (2013) ሲገልጹ የዘመንን አቆጣጠር ከሚቶሎጂ ጋር የሚያገናኘዉ ዋናዉ ጉዳይ፣ የሰዉ ሌጅ ለዘመን ምልክትነት የተሰጡትን አዉደ ከዋክብት በሚወጡበትና በሚገቡበት ክፍለ ጊዜያት አንፃር የሚከሰቱትን የተለያዩ ምድራዊ ጠባያትና ሁነቶች በማጤንና የክስተቶቹንም ድግግሞሽ በየአይነታቸዉ በመለማመድ፤ አካላዊ ገጽታ እየፈጠረላቸዉና የባህርይ ወካይ ስያሜ ከመስጠት አልፎ ዘመናቸዉን የሚያሳዉቅ አይረሴ አፈ-ታሪኮችን ያበጀላቸዉ በመሆኑ ነዉ፡፡ አፈታሪኮቹም የፈጠራ ቢሆኑም፤ ከዋክብቶቹ የሚወጡበት ዘመን በቀላል ተለይቶ የሚታወቁበት ቋሚ የአቆጣጠር ዘዴ ወይም ወቅቶችን የመለየት ልማድ እየዳበረ እንዲመጣ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በአጠቃላይ፤ የሰዉ ልጅ ዓመታዊ ዙሩም መጀመሩን ወይም መጠናቀቁን በቀላል መለየትን የተለማመደበት ተረክ በመሆኑ፤ በአዉደ-ከዋክብት አቆጣጠር /Sidereal Calendar/ ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ማሳረፍ የቻለና በብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ ባህል ሆኖ የቀጠለ ነዉ ይላሉ፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የዳውሮ ብሔረሰብ የዘመን አቆጣጠን ከዚህ ፅንሰ ሃሳብ አንፃር ምን ያህል የሚጋራዉ እሴቶች እንዳሉት የምናይ ነዉ የሚሆነው፡፡

### 2.1.4. የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት

The Ethiopian Messenger (17 - August-October 2020) ሲገልጽ በኢትዮጵያዊያንም ሆነ በአውሮፓዊያን ቀን አቆጣጠር መሠረት የዓመት ርዝማኔው 365 ቀን ከሩብ ነው። ሁለቱም ሀገሮች መነሻ ያደረጉት ክርስቶስ የተወለደበትን ዓመት ነው።

የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት እንዲሁም እንቁጣጣሽ በመባል የሚታወቀው መስከረም 1 ቀን ይከበራል። ኢትዮጵያ የሰው ልጆች መገኛና የቡና መገኛ ከመሆኗ በተጨማሪ የራሳቸው ፊደልና የዘመን አቆጣጠር ካላቸው ጥቂት ጥንታዊ ሥልጣኔዎች አንዷ ነች። እንደ ጎርጎርያን ካላንደር የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 13 ወራት ያሉት ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ 12 ወሩ እያንዳንዳቸው 30 ቀናት ያሉት ሲሆን ጳጉሜን የምትባለው 13ኛው ወር በመደበኛነት አምስት ቀናት ትኖራለች። ነገር ግን በየአራት አመቱ ወደ ስድስት ቀናት ይቀየራል። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ከጥቂት አመታት በፊት በ"Land of Origins" ከመተካቷ በፊት የሀገሪቱ ይፋዊ እና ታዋቂ የቱሪዝም መፈክር የነበረችው "የአስራ ሶስት ወር የፀሀይ ብርሀን" ሀገር ተብላ ትታወቅ ነበር። አዲሱ ዓመት የሚጀምረው በጥር ወር ሳይሆን በመስከረም (መስከረም በአገር ውስጥ ቋንቋ) ነው በማለት ያብራራል።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ የመስከረም ወር የዘመን መለወጫ መጀመሩን የሚገልጹ ልዩ ልዩ ምልክቶች እንደሚታዩ ይታመናል። ለምሳሌ አበባዎች በየቦታው የሚታዩበት ጊዜ፣ ጭጋጋማ እና ከባድ የዝናብ ወቅት የሰኔ፣ የሐምሌ እና የነሐሴ ወር ማብቂያ እና አስደሳች ፀሐያማ ነው። በአዲስ መንፈስ እና ጉልበት ደስተኛ እና አዲስ ጅምርን የሚያመለክት ጊዜ ይጀምራል ሲል (The Ethiopian Messenger 17 - August-October 2020) ይገልጻል፡፡

አሁን ያለው የኢትዮጵያ አቆጣጠር ከጎርጎሪዮሳዊው የዘመን አቆጣጠር በሰባት ዓመት ከስምንት ወር ይዘገያል። ምንም እንኳን የግሪጎሪያን ካላንደር በአለም ላይ በብዛት ጥቅም ላይ የዋለ ቢሆንም ዓመተ ምህረት የዘመን አቆጣጠር የተጀመረው ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ እንደሆነ ይገመታል። ኢትዮጵያውያን ግን ትክክለኛው የቆጠራ መንገድ በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ የዋለው የቀን መቁጠሪያ ነው ሲሉ ይከራከራሉ።

በኢትዮጵያ አቆጣጠር የመጀመሪያ ቀን መስከረም 1 በአገር ውስጥ ቋንቋ እንቁጣጣሽ በመባል ትታወቃለች። ትርጉሙም በአፈ ታሪክ እንደተገለጸው 'የጌጣጌጥ ስጦታ' ማለት ነው። አፈ ታሪኩ ሁለት የተለያዩ ግን ተዛማጅ ትረካዎችን ያሳያል። የመጀመሪያው የኢየሩሳሌም ንጉሥ ሰሎሞን በ980 ዓ.ዓ አካባቢ ኢየሩሳሌምን ባደረገችው ታሪካዊ ጉብኝት ከ3,000 ዓመታት በፊት ለንግስት ሳባ የአልማዝ ቀለበት ሰጣት። ስጦታውን ተቀብላ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰችው በመስከረም ወር ከሚከበረው የዘመን መለወጫ በዓል ጋር በመገጣጠም እንቁጣጣሽ የሚለው ስያሜ መጣ። ሌላው ትረካ ንግሥተ ሳባ በኢየሩሳሌም ንጉሥ ሰሎሞንን ጎብኝታ ስትመለስ ወደ ኢትዮጵያ ስትመለስ አለቆቿ ግምጃ ቤቷን የአልማዝ እና ሌሎች ውድ ማዕድናት በመሙላት እንደተቀበሏት ይናገራል በማለት (The Ethiopian Messenger 17 - August-October 2020) ያስረዳል፡፡

ኢትዮጵያ አዲስ አመቷን በዚህ ወር የምታከብርበት አንዱ ምክንያት በመስከረም 23 አካባቢ የመጸው እኩልነት ስለሚከሰት የቀን እና የሌሊት ሰአት ቁጥር በአለም ዙሪያ በትክክል እኩል ይሆናል የሚል እምነት ነው። በኢትዮጵያ የፀሃይ አቆጣጠር ጊዜን ለመቁጠር የሚያገለግሉት ፀሀይ እና ጨረቃ እያንዳንዳቸው ከመውጣታቸው በፊት 12 ሰአት አላቸው። ሁለተኛው ምክንያት የሰማያትና የምድር ፍጥረት የተከናወነው በመስከረም ወር ነው ከሚል ሃይማኖታዊ እምነት የተወሰደ ነው።

ይህ በዓል ለወጣት ልጃገረዶች እና ወንድ ልጆች ቀኑን በጉጉት ሲጠባበቁ አበባየሆሽ የተሰኘውን አስደናቂ ባህላዊ ዜማ በተለይም ወደ አካባቢያቸው እና ቤተሰባቸው ቀርበው ለአዲሱ መልካም ምኞት መግለጫ የሚቀርቡ ልጃገረዶች ልዩ ስሜት ይፈጥራል። በዓመት እና በምላሹ ከሽማግሌዎች በረከት ያገኛሉ። በአዲሱ ዓመት ማለዳ ላይ ልጃገረዶች በዘፈንና በአስደሳች ከበሮ እየታፈሱ ወደሚሄዱ ሰዎች ሲቀርቡ በጣም አስደናቂ ነው። አደይ አበባ በመባል የሚታወቁትን ደማቅ ቢጫ አበባዎችን ይይዛሉ፤ እነዚህም በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ። በዓሉ መላውን ቤተሰብ ያሳተፈ በመሆኑ፣ ልጃገረዶች በመዘመር ላይ እያሉ፣ ወንዶቹ አዲስ ብሩህ ቀን መምጣቱን የሚያበስሩ ውብ ሥዕሎችን በመስራት በበዓል ጧት ከቤት ወደ ቤት እየዞሩ የጥበብ ሥራዎቻቸውን ለዘመዶች፣ ለጎረቤቶች እና ለንደኞች ይሰጣሉ። ከልጆች ለቀጣዩ አመት የመልካም እድል ምስጋናዎችን ከተቀበሉ በኂላ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለበዓል ወይም ለሌላ የምስጋና መግለጫዎች በተዘጋጀ የቤት ውስጥ ባህላዊ ዳቦ ምላሽ

ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ህዝቡ በባህላዊ አልባሳት ያጌጠ ሲሆን ታዋቂውን የቡና ስነ ስርዓት ጨምሮ የባህል ምግቦች እና መጠጦች በሁሉም ሰው ቤት ይቀርባሉ እንዲሁም ዘመዶች፣ ጎረቤቶች እና ወዳጆች ወደ ቤት ይጋበዛሉ፡፡ ሰዎች ከሚወዷቸው ጋር ስጦታዎችን እና መልካም ምኞቶችን ይለዋወጣሉ፡፡

የኢትዮጵያ አዲስ አመት ብቻውን አይመጣም፡፡ ከአዲሱ ዓመት በፊት እና በኋላ የሚከበሩ ሌሎች ባህላዊ እና ከፊል ሃይማኖታዊ በዓላትም አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል አሸንዳ/ሻደይ፣ የመስቀል በዓል እና የኢሬቻ በዓል ይገኙበታል (The Ethiopian Messenger 17 - August-October 2020)፡፡

ዲያቆን ዘአማኑኤል (2009) በዓል ማለት ‹‹አብዐለ - አከበረ›› ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ‹‹መታሰቢያ ማድረግ፣ ማክበር›› ማለት ነው፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም በመዝገበ ቃላታቸው ‹‹በዓል (ላት) በቁሙ፣ የደስታ፣ የዕረፍት ቀን፤ በዓመት፣ በወር፣ በሳምንት የሚከበር፤ ያለፈ ነገር የሚታሰብበት፤ ሕዝብ የበዓሉን ምሥጢር እያሰበ ደስ ብሎት እና ለብሶ፣ አጊጦ የሚዘፍንበት የሚዘምርበት፤ እልል የሚልበት፤ ሽብሽባ፣ ጭብጨባ የሚያደርግበት፤ ሲያረግድ እስክስታ ሲወርድ ባንገቱ የሚቀጭበት እንደ ጥጃ የሚፈነጭበት ነው›› በማለት የበዓልን ትርጉም ገልጸውታል፡፡ በአጠቃላይ በዓል ማለት ማሰብ፣ መዘከር፣ ማስታወስ የሚል ትርጉም አለው፡፡

ዘመን መለወጫ የኢትዮጵያ የወራት ሁሉ መጀመሪያ መስከረም ነው፡፡ ይህ ወር ዘመን መለወጫ፣ ዕንቁጣጣሽ፣ ቅዱስ ዮሐንስ እየተባለ ይጠራል፡፡ ስለ አዲስ ዓመት በተለያየ ስም የመጠራቱ ታሪካዊ አመጣጥና ስያሜ መነሻ ሃሳቡ ምን እንደሆነ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡ ዘመን መለወጫ መስከረም ወር የሆነበት ምክንያት "ብርሃናት /ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት/የዓመት ዑደታቸውን በጳጉሜ ወር ጨርሰው በመስከረም ወር ስለሚጀምሩ ነው፡፡ ሌሊቱ ከቀኑ ጋር ይተካከላል፡፡ ዓመቱን ጠንቅቀው ቢቆጥሩ 365 ቀናት ይሆናል፡፡ "ሌሊቱም ከቀኑ ጋራ ይተካከላል፡፡ ዓመቱም ጠንቅቆ ቢቆጥሩት ሦስት መቶ ስልሳ አራት ቀን ይሆናል፡፡ በዘመነ ኖኅ ዓለምን ንፍር ውኃ አጥለቅልቆት ከቆየ በኋላ ዳግመኛ ውኃው የጎደለበት በመሆኑ ዕንቁጣጣሽ የተባለበት ምክንያት አንደኛ "ዕንቍ ዕፅ አመጣሽ" ብሎ የአበባውን መፈንዳት ያመለክታል፡፡ ሁለተኛ ኖኅ ለሦስቱ ልጆቹ አህጉራትን በእጣ ሲያካፍላቸው አፍሪካ ለካም ደረሰችው፡፡ በአፍሪካ ምድርም ሲገባ በመጀመሪያ

ያረፈው በኢትዮጵያ ነበር። ሀገሪቱም በአደይ አበባ አሸብርቃ ነበር። ወሩ ወርኀ መስከረም በመሆኑ ደስ ብሎት ዕንቁ ዕጣ ወጣሽልኝ በማለት ይህችን ወቅት እንቁጣጣሽ ብሏታል። ሦስተኛው አዜብ የንጉሡን ጥበብ ከመስማት ማየትን መርጣ ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ከብዙ ሠራዊቶቿ ጋር የእጅ መንሻ በመያዝ ሄደች። ንጉሡም በደስታ ተቀብሎ እርሱም "እንቁ ለጣትሽ ጌጥ ይሁንሽ" በማለት አራት አይነት ቀለም የሚታይበት በቀንና በሌሊት የሚያበራ ቀለበት ሰጥቷታል። ወሩም ወርኀ መስከረም ነበር። ከዚህ በመነሣት እንቁጣጣሽ የሚለው ስያሜ ወጥቷል። ቅዱስ ዮሐንስ ሦስተኛው የአዲስ ዘመን ስያሜ ቅዱስ ዮሐንስ ነው። የመጥምቁ ዮሐንስ ተግባር ለዘመነ ወንጌል በር ወይም መነሻ እንዲሆን ለኢትዮጵያ ዐውደ ዓመት መስከረም አንድ ቀን እንዲከበር ሆኗል።

### 2.1.5. የአዲስ ዓመት ዋዜማ

Staf (2016) በብዙ አገሮች የአዲስ ዓመት በዓላት በአሮጌው ዓመት መጨረሻ ምሽት ይጀምራሉ። የአዲስ ዓመት ዋዜማ እስከ አዲስ ዓመት 1 መጀመሪያ ሰዓታት ድረስ ይቀጥላሉ። ሰዎችም ብዙውን ጊዜ በሚመጣው ዓመት መልካም ዕድል ያመጣሉ ተብሎ በሚታሰቡ ምግቦች እና መጠጦች ይደሰታሉ። ለምሳሌ፡- በስፔንና በሌሎች በርካታ የስፓኒሽ ተናጋሪ አገሮች ሰዎች ከእኩለ ሌሊት በፊት አሥራ ሁለት የወይን ፍሬዎችን አዘጋጅተው ይመገባሉ። የወይኑ ፍሬዎች ወደፊት ለሚመጡት ወራት ያላቸውን ተስፋ ያመለክታሉ የሚል እምነትም አላቸው። ባህላዊ የአዲስ ዓመት ምግቦች እንደ ባቄላ እና አተር ያሉ ጥራጥሬዎችን ይመገባሉ።

በዓለም ዙሪያ የተለመዱት ሌሎች ልማዶች አዲሱን ዓመት ለመቀበል ርችቶችን መመልከት እና ዘፈኖችን መዘመር ያካትታሉ። ለአዲሱ ዓመት ዕቅዶችን የማውጣት ልማድ በመጀመሪያ በጥንቶቹ ባቢሎናውያን ውስጥ እንደተጀመረ ይገመታል።

## 2.2. የቀን አቆጣጠር በተለያዩ ሀገሮች

በጥንት ስልጣኔያቸው የታወቁት ለምሳሌ፡- ግሪኮች፣ ሮማዊያን፣ ባቢሎናዊያን፣ እብራዊያን፣ የቻይና ሰዎች አቆጣጠራቸው የተመሠረተው ጨረቃ በመሬት ዙሪያ ከምታደርገው መሽከርከር ወይም በተራ አነጋገር ከጨረቃ መታየት ጋር ነው። ስለሆነም የወራት ሂደት ወይም የቀን አቆጣጠር ጋር አልገናኝ እያሉ ይፈጠር

የነበረውን ችግር ለመቋቋም ተጨማሪ ቀኖች አልፎ አልፎ በአስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲገቡ ይደረግ ነበር፡፡

የዘመን አቆጣጠር በየአገሩ የራሱ ታሪክ ያለው ነው፡፡ ቁጥሩን የሚወስኑት ቆጠራው የተጀመረበት ዓመትና አቆጣጠሩ የተመሠረተው በጨረቃ ወይም በጸሃይ እሽክርክሪት ላይ መሆን አለመሆን ናቸው (ታደሰ 2000)፡፡

### 2.2.1. የዘመን አቆጣጠር ሚቶሎጂያዊ ዳራ

የዘመንን አቆጣጠር ከሚቶሎጂ ጋር የሚያገናኘዉ ዋናዉ ጉዳይ፣ የሰዉ ልጅ ለዘመን ምልክትነት የተሰጡትን ዓዉደ ከዋክብት በሚወጡበትና በሚገቡበት ክፍለ ጊዜያት አንፃር የሚከሰቱትን የተለያዩ ምድራዊ ጠባያትና ሁነቶች በማጤንና የክስተቶቹንም ድግግሞሽ በየአይነታቸዉ በመለማመድ፤ አካላዊ ገጽታ እየፈጠረላቸዉና የባህርይ ወካይ ስያሜ ከመስጠት አልፎ ዘመናቸዉን የሚያሳዉቅ አይረሴ አፈ-ታሪኮችን ያበጀላቸዉ በመሆኑ ነዉ፡፡ አፈ-ታሪኮቹም የፈጠራ ቢሆኑም፤ ከዋክብቶቹ የሚወጡበት ዘመን በቀላል ተለይቶ የሚታወቁበት ቋሚ የአቆጣጠር ዘዴ ወይም ወቅቶችን የመለየት ልማድ እየዳበረ እንዲመጣ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በአጠቃላይ፤ የሰዉ ልጅ ዓመታዊ ዙሩም መጀመሩን ወይም መጠናቀቁን በቀላል መለየትን የተለማመደበት ተረክ በመሆኑ፤ ካየናቸዉ አራቱ የአቆጣጠር ዓይነቶች ዉስጥ፣ በዓዉደ-ከዋክብት አቆጣጠር /Sidereal Calendar/ ላይ ቀጥተኛ 34 ተፅዕኖ ማሳረፍ የቻለና በብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ ባህል ሆኖ የቀጠለ ነዉ፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ጨረቃን መሠረት ያደረገ አቆጣጠር ከዚህ ፅንሰ ሃሳብ አንፃር ምን ያህል የሚጋራዉ እሴት እንዳለዉ የምናይበት ክፍል ነዉ፡፡

### 2.2.2. የጥንት ግብጽ ዘመን አቆጣጠር

ስለግብጻዊያን ዘመን አቆጣጠር ታደሰ (2000) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

የእርሻ ጥበብ ካዳበሩትና ለስልጣኔ ዋና ምንጭ ከነበሩት ህዝቦች መካከል ግብጻዊያን በግንባር ቀደም የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንግሊዞች necessity is the mother of invention እንዳሉት ጥንት ግብጻዊያን በእርሻ ሥራ የተራቀቁት ለዝናብ ስላልታደሉና ሳይተርፋት አበደረች እንዲሉ እናታቸው ኢትዮጵያ የምትልክላቸውን ውሃና አፈር በቅጡ ከመጠቀም ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው ስለተገነዘቡ ነበር፡፡
የጥንት ግብጻዊያን የቀን አቆጣጠራቸው የተመሰረተው ከእርሻ ሥራ ጋር የተቆራኘ ነበር፡፡ ይኸውም አቆጣጠራቸው የወራት መፈራረቅን አንጸባራቂ ነበር፡፡ በዘመናዊ አነጋገር

አቆጣጠሩ መሬት በጸሃይ ዙሪያ ከምታደርገው መሽከርከር ጋር የተቆራኘ ነበር፡፡ በግብጽ ዓመቱ 12 ወሮች፣ እያንዳንዱ ወር ደግሞ 30 ቀናት እንዲኖሩት ተደርጎ ለረጅም ጊዜ ሲሰራበት ከቆየ በኂላ በጋና ክረምት በአሳቻ ወቅት ከተፍ እያሉባቸው ስለተቸገሩ ስለከዋክብት እንቅስቃሴ ጥልቅ ምርምር ለማድረግ ተነሳሱ፡፡ ውጤቱም 6000 ዓመት ገደማ የአምስት ቀኖች መጨመር ነበር፡፡ ተጨማሪዎቹ ቀኖች ለታላላቆቹ አማልክቶቻቸው እንዲሆኑ ተወስኖ የአባይ ውሃ ሞልቶ መምጣት በታላቅ ጉጉት እየተጠበቀ አምስቱን ቀኖች ህዝቡ በፈንጠዝያና በጸሎት ያሳልፋቸው ነበር፡፡

የጥንት ግብጻዊያን ሳያሰልስ የህይወት መሠረት የሆነውን ውሃና ምዕራባዊያን የኢትዮጵያ ክፍል በማራቆት በየዓመቱ 30 ቢሊዮን ኩንታል ያህል አፈር ተሸክሞ ከተፍ የሚልበትን ወር የወሮች ሁሉ መጀመሪያ ወይም በኩር አደረጉት፡፡ ስሙም ቱት ይባላል፡፡ የግብጾች ዓመት ብሎም ቱት የሚጀምረው በኢትዮጵያ አቆጣጠር መስከረም አንድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር ከየት እንደመጣ ከወዲሁ መገመት ይቻላል፡፡

የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ግብጽን የዛሬ 1400 ዓመት ገደማ ከወረሩ በኂላ ግን ከ 5000 ዓመት በላይ የተሠራበት የቀን መቁጠሪያ ውድቅ ተደርጎ ወደ ጨረቃ ማንጋጠጥ ተጀመረ፡፡

### 2.2.3. የጁሊያን ካላንደር

ታደሰ (2000) ሲገልጹ "ጁሊየስ ሲዘር የሮማዊያን ቀን አቆጣጠር መሠረቱን ከጨረቃ ወደ ጸሃይ እሽክርክሪት እንዲዞር አደረገው፡፡ ይህ የሆነው እ.ኤ.አ. ከክርስቶስ ልደት በፊት በ46 ነበር፡፡ ግብጾች ይከተሉት ወደነበረው ስርዓት አዞሩት ማለት ነው፡፡ ሌሎች ተጨማሪ እርምጃዎችንም ወሰደ፡-

አንደኛ፡- መሬት በጸሃይ ዙሪያ ለመሽከርከር የሚፈጅባት ጊዜ 365 ቀኖች ከስድስት ሰዓት መሆኑን ተገንዝቦ (ትክክለኛው ጊዜ 365 ቀን፣ ስድስት ሰዓት፣ 11 ደቂቃ ከ15 ሴኮንድ ነው) የወራት መዛነፍን ለማስቀረት በየአራቱ ዓመት አንድ ቀን እንዲጨምር አዘዘ፡፡ አንድ ዓመት 365 ቀኖች ብቻ ሳይሆን 365 ከሩብ እንዳሉት ጁሊየስ ሲዘር የተረዳው ከግብጽ የከዋክብት ተመራማሪዎች ነው፡፡ የግብጽ ሰዎች ግኝቱን ወደተሻሻለ ቀን አቆጣጠር ሳይተረጉሙት በመቅረታቸው ጁሊየስ ሲዘር እርምጃ ወስዶ ስሙን አስተካከለበት፡፡

ሁለተኛ፡- የግብጾችን አስራ ሶስተኛ ቁንጽል ወር አስቀርቶ አራት ወሮች እያንዳንዳቸው 30 ቀን፣ ሰባት ወሮች 31 ቀን እንዲኖራቸው አደረገና አስራ ሁለተኛው ወር ለሦስት ተከታታይ ዓመታት 28 ቀኖች፣ በአራተኛው ዓመት ደግሞ 29 ቀኖች እንዲኖሩ አደረገ፡፡"

### 2.2.4. ግርጎሪያን ካላንደር

ታደሰ (2000) "ወደ ጁሊየስ ሲዘር ቀን አቆጣጠር ስንመለስ በየአራቱ ዓመት አንድ ቀን ይጨምር የተባለው ድንጋጌ በትክክል ሥራ ላይ ሳይውል ቀረ። ጭማሪው በየሶስት ዓመት ሆነና ውዥንብር ተፈጠረ። ቤተክርስቲያናት እ.ኤ.አ. በ 325 በኒቂያው ጉባኤ አንድ ወጥ ካላንደር ቢያጸድቁም በትክክል በተግባር ሳይተረጎም ቀረ።

የተሻሻለ ነው የተባለው ሌላ ካላንደር የሮማው ቤተክርስቲያን እ.ኤ.አ. በ 530 አወጣ። ለማሻሻያው መሠረት የነበረው ዳዮኒስየስ የተባለው መነኩሴ ያደረጉት የዘመን ስሌት ነበር። የቀን መቁጠሪያው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በሚያዝናቸው ወይም በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች በጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ የመነኩሴው ስሌት ክርስቶስ የተወለደበትን ዘመን ቢያንስ በሰባት ዓመት እንዳስረዘመው ተደረሰበት። ይህ ስለመሆኑ ወይም ስህተት ስለመፈጸሙ በሊቃውንትና በቤተክርስቲያን ሰዎች መካከል መተማመን ነበር። ለስህተቱ እንደጉልህ ማስረጃ የተጠቀሰው፡-

አንድኛ፡- ቤተክርስቲያን ክርስቶስ በተወለደበት ዓመት አዲስ ከዋክበክብት ታዩ እያለች ተሻሻለ እንደተባለው የቀን መቁጠሪያ ከሆነ ግን ኮከቦቹ የታዩበትን ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በሰባት ዓመት ያስቀድመዋል። በነገራችን ላይ የከዋከብት ተመራማሪዎች እንደደረሱበት ታዩ የተባሉት ኮከቦች ጁፒተርና ሳተርን ናቸው። ያለወትሮው ተረጋግተውና ቦግ ብለው መታየታቸው ከክርስቶስ መወለድ ጋር ተገጣጠመ።

ሁለተኛ፡- ክርስቶስ በተወለደበት ዓመት የአይሁድ ህጻናት እንዲፈጁ ትዕዛዝ ያስተላፈው ንጉስ ሄሮድስ ሆኖ ሳለ ተሻሻለ የተባለው የዘመን መቁጠሪያ ግን የንጉሱን ሞት ከክርስቶስ ልደት በአራት ዓመት ያስቀድመዋል።

የፋስካን በዓል አከባበር በተመለከተ በዓሉ የሚከበርበት ቀን እንደዘመን አቆጣጠሩ እየተዘበራረቀ ተቸግረው ስለነበር ጉዳዩ ያሳሰባቸው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አባቶች ለረጅም ጊዜ የመፍትሔ ሀሳቦችን ሲያንከባልሉ፣ ሲያነሱና ሲጥሉ ከቆዩ በኋላ እ.ኤ.አ. በ1582 ዓ.ም የሮማው ጳጳስ ጎርጎርዮስ አስራ ሶስተኛው (Gregory XIII) ለሁሉም ክርስቲኖች የሚያገለግልና በጊዜው የነበሩትን ውዥንብሮች የሚያስወግ አዲስ የዘመን አቆጣጠር ስርዓትና የበዓላት ቀኖች የሚቀመሩበት ዘዴ አውጥቻለሁና አይታችሁ አጽድቁልኝ ብሎ በመላው ዓለም ለሚገኙ የቤተክርስቲያኑ ተጠሪዎች የስብሰባ ጥሪ አስተላለፈ። ከጎርጎርዮስ ሀሳቦች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ፡-

አንደኛ፡- በ 1582 ከነበረው የኦክቶበር ወር አስር ቀኖች እንደሌሉ እንዲቆጠር ሆኖ ቀኖች እንዲሸነሸኑ፣

ሁለተኛ፡- የፋሲካ በዓል የሚከበርበት ቀን ሳይዘበራረቅ ሁሉም በአንድ ቀን ማክበር እንዲችል የወጣውን አዲስ የቀን የመቀመሪያ ዘዴ ሁሉም እንዲከተለው፣

ከ1600 ዓመት ዓመት በፊት ጁሊየስ ሲዘር የደነገገው በየአራቱ ዓመት የአንድ ቀን ጭማሪ ተግባራዊ እንዲሆን፣

ሦስተኛ፡- 1582ን ሁሉም መነሻ አድርጎት ወደፊት እንዲጓዝ የሚሉትና ለጉባኤው የቀረቡት ሀሳቦች ተቀባይነት አግኝተው ጸደቁ። ውጤቱም አሁን የአውሮፓዊያን ዘመን አቆጣጠር ወይም ግሪጎሪያን ካላንደር የምንለው ነው።"

ከላይ ያሉትን የተለያዩ ሀገራት ዘመን አቆጣጠራቸውንና የየሀገራቱን አዲስ ዓመት በዓል አከባበራቸውን ስንመለከት ሀገራቱ በአሮጌው ዓመት መጨረሻ ላይ የሚያከብሩት መሆናቸው እና በጨረቃ እንቅስቃሴ መሠረት የሚያደርጉት መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። ይህ ደግሞ የዳውሮ ብሔርሰብ የቶክ ቤኣ በዓል ከሚያከብሩት ጋር የሚያገናኛቸው መሆኑን እንድንገነዘብ ያስችለናል።

## 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ክፍል የሚዳስሰው በተለያዩ ጊዜያት በልዩ ልዩ ጥናትና ተመራማሪዎች ዘንድ የተሰራ የተዛማጅ ስራዎችን በመፈተሽ ግንኙነታቸው ላይና ልዩነታቸው ላይ ያተኩራል።

በዚህ ጥናት አስፋው (2013) የኢትዮጵያዊያንና የጎርጎሮሳዊያን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት ምንጭ፡ የሄኖክን የብርሀናት ነገር እና ባሕረ-ሀሳብን ተተኪሪ ያደረገ ጥናታዊ ዳሰሳ በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል፣ የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ለድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የተካሄደ ጥናታዊ ጽሑፍ የተዳሰሰ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ተመሳስሎና ልዩነት ተብራርቶ ቀርቧል።

ምንም እንኳ የዘመን አቆጣጠርን መሠረት ያደረገ በመሆኑና ጨረቃን በመጠቀም ዘመንን የመቁጠር ጥበብ፣ ተንታኝ ገላጭ የጥናት ንድፍ መጠቀሙ፣ የሁለቱም መረጃ መተንተኛ ዘዴ አይነታዊ በመሆኑ፣ ሰነድ ፍተሻን በመረጃ መሰብሰቢያነት መጋራቱ የሚያመሳስላቸው በመሆኑ ለዚህ ጥናት በመረጃነት የሚያገለግል ቢሆንም

ይዞት ከተነሳው ዓላማ፣ ከተጠናበት ጊዜና ቦታ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን ሰነድ ፍተሻ ብቻ የተጠቀመ በመሆኑ ከዚህ ጥናት የሚለያይ ይሆናል፡፡

ሌላው ይህ ሥራ የዘመን መለወጫውን ክወና ስርዓት የሚተነትን ሲሆን የአስፋው ሥራ በኢትዮጵያዊያን እና በጎርጎሮሳዊያን የዘመን አቆጣጠር መካከል ባለዉ የዘመን ቁጥር ልዩነት ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ ልዩ የሚያደርጉት ጉዳዮች ናቸው፡፡

Daimo (2020) "Tookibe'a- The Cultural Event of The New Year Celebration Among The Dawuro, South West Ethiopia" በሚል ርዕስ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስ፣ በአንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ሌላው በዚህ ጥናት ዳሰሳ የተደረገበት ሲሆን ጥናቱን ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስሉት ጉዳዮች ገላጭ የጥናት ንድፍ የተጠቀመ መሆኑ፣ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ቃለ መጠይቅን የተጠቀመ መሆኑ እና በተመሳሳይ ገና ወረዳን በተተኳሪነት የጥናቱ ቦታ ማድረጉ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ልዩ የሚያደርጉት ጉዳዮች ደግሞ የተጠናበት ወቅት፣ በመረጃ መሰብሰቢያነት ቡድን ተኮር ውይይትንና ምልከታ በተፈጥሯዊ መቼት መጠቀሙ፣ የጥናቱ ተተኳሪ ወረዳዎችን ኢሰራ፣ ቶጫ እና ታርጫ ዙሪያ ወረዳዎችን ማድረጉ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በተጨማሪ ዳዕሞ በጥናቱ ውስጥ የዳውሮ ብሔረሰብ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቶችንና የጎሳዎችን ዝርዝር ልዩነት ያካተተ ሲሆን ይህ ጥናት እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች ያላካተተ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

Seid (2007)" A Historical Survey of Dawuro, Southwest Ethiopia (Up to 1974)" በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ማሟያ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸው የዳውሮ ብሔረሰብ ዘመን መለወጫ በዓል እንደ አንድ የጥናቱ ቅኝት አካል ያደረጉ ሲሆን በገላጭ የምርምር ዘዴ ትንተና ማድረጋቸው፣ መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀሙባቸው ዘዴዎች ሰነድ ፍተሻና ቃለመጠይቅ መሆኑ ከዚህ ሥራ ጋር የሚያመሳስለው ሲሆን ሰይድ በጥናታቸው ሌሎችንም ባህሎች በማካተት የዘመን መለወጫ በዓልን እንደ አንድ የብሔሩ ባህላዊ ቅርስ አድርገው አቀረቡ እንጂ ለብቻው አድርገው ሰፊ ማብራሪያ ያላቀረቡ መሆናቸው፣ ለጥናቱ መረጃ ምንጭነት የተጠቀሙባቸው ወረዳዎች

የተለያየ መሆን፣ ጥናቱ የተካሄደበት ዘመን፣ ለመረጃ ምንጭነት ተሳታፊ ለመምረጥ የተጠቀሙበት ናሙና ከዚህ ሥራ እንዲለያይ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

እንደ አጠቃላይ ከዚህ የጥናት ርዕስ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች በስፋት ለማግኘት ባይቻልም የተዳሰሱትን ከፍ ሲል በተብራራው መልክ ግንኙነታቸውና ልዩነታቸውም ቀርቧል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

ምዕራፍ ሶሰት ጥናቱ በምን ዘዴ ትንተና እንደሚደረግ፣ መረጃ ከማንና ከየት እንደሚገኝ ፣ መረጃ በምን ዘዴ እንደሚገኝ የሚገለጽበት ክፍል እንደመሆኑ የጥናቱ ንድፍ፣ የመረጃ ምንጮች፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ አደረጃጀት እና የመረጃ መተንተኛ ዘዴ የሚሉ ርዕሶች ከነማብራሪያቸው በዚህ ክፍል ቀርበዋል፡፡

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የዳውሮ ብሔረሰብ የቶክ ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል ክወና ሥርዓት መተንተን ሲሆን ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አገልግሎት ላይ የዋለው የጥናት ንድፍ ገላጭ ተንታኝ የምርምር ንድፍ (Descriptive Analytical research method) ነው፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምክንያት ገለፃ በትንታኔ ወቅት የምናስቀድመው ተግባር ሲሆን እኛ ያየነውን ክዋኔ ያላዩት ሰዎች በአእምሯቸው እንዲቀርፁት ማድረግ ስለሚያስችል ነው፡፡ በተጨማሪም በተፈጥሮአዊ መቼቶች በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ትንታኔ ለመስጠት ስለሚረዳ ነው፡፡ "የገላጭ የምርምር ዘዴ ሂደት ተፈጥሯዊ መልክ ያለው ሲሆን ምልከታ በማካሄድም ያዩትን መመዝገብ፣ የመዘገቡትን በተገቢው መንገድ መግለፅን ያካትታል" (ያለው፣1998፣21)፡፡

### 3.2. የመረጃ ምንጮች

ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ መረጃዎች ከቀዳማይ መረጃ ምንጮችና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስቧል፡፡ በቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት የጥናቱ ትኩረት የሆኑት በዳውሮ ዞን ገና ወረዳ እና ታርጫ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ በናሙና የተመረጡ የማህበረሰብ ክፍሎች ሲሆኑ፤ በቃለ መጠይቅ ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በቀዳማይ የመረጃ ምንጭነት ከብሔረሰቡ ውስጥ ስለበዓሉ እውቀት ያላቸው 10 (አስር) ከተለያየ ማህበረሰብ ክፍል የተውጣጡ ሰዎች በዓላማ ተኮር ዘዴ ተመርጠው መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ከካልዓይ የመረጃ ምንጭነት ደግሞ በሰነድ ፍተሻ ከዚህ ቀደም በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተጻፉ ጽሑፎችን በመቃኘት፣ የተለያዩ መጻሕፍትን፣ ጆርናሎችን እና መዛግብትን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች

### 3.3.1. የጥናቱ ቦታ ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ በዳውሮ ዞን ውስጥ ካሉት አስር (10) ወረዳዎችና ሁለት (2) ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በገና ወረዳ እና በታርጫ ከተማ አስተዳደር የተካሄደ እንደሆነ ቀደም ሲል በጥናቱ ወሰን ክፍል ተገልጿል፡፡ ገና ወረዳ እና ታርጫ ከተማ አስተዳደር ለጥናቱ የተመረጡት በአመቺ ናሙና ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ገና ወረዳ አጥኚው የሚኖርበት አካባቢ በመሆኑ ለመረጃ ሥራ አመቺ ሆኖ ስለተገኘ ሲሆን ታርጫ ከተማ አስተዳደር የተመረጠበት ምክንያት የዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ እዚያው የሚገኝ በመሆኑ ለመረጃ ምንጭነት የተመረጡ የዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያዎችን ለማግኘት ታስቦ ነው፡፡

### 3.3.2. የመረጃ ሰጪዎች ናሙና አመራረጥ

የዳውሮ ብሔረሰብ ቶክ ቤኣ በዓል ክወናን ለመተንተን ተገቢ የሆነውን መረጃው ከተጠኚ ማህበረሰብ ክፍል መሰብሰብ ጠቃሚ ስለሆነና የተሻለ ውጤት ለማግኘት ስለሚያስችል በቂ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የታመኑ የበዓሉን ታሪክ ሊያብራሩ የሚችሉ ከዳውሮ ብሄር አካባቢ ሽማግሌዎች ሦስት (3)፣ ከቤት እመቤቶች ሁለት (2)፣ በዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ ከሚሠሩ ባለሙያዎች አምስት (5) በድምሩ አስር (10) መረጃ አቃባዮች በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመረጃ ምንጭነት ተመርጠዋል፡፡

ናሙና አመራረጥ ዘዴ ዓላማ ተኮር ዘዴን ለመጠቀም የተፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ሁሉም የብሔሩ ተወላጆች ስለበዓሉ አከባበርና በበዓሉ ስለሚፈጸሙ ክወናዎች እኩል እውቀት ላይኖራቸው ስለሚችል በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ የተመረጡ ከእነዚህ መረጃ ሰጪዎች ታማኝ መረጃዎችን ለማግኘት ስለታሰበ ነው፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማሰባሰብ መፍትሔ ለማፈላለግም ሆነ ችግሮችን በሂደት

እየፈቱ ለመሄድ ተገቢና በቂ መረጃ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን መረጃ ለማግኘት ደግሞ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በጥንቃቄ መሰብሰብ አለበት፡፡ ለዚህም የተለያዩ ዘዴዎች ስላሉ

እንደ ጥናት አይነቱ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ለጥናታዊ ምርምር የሚያስፈልጉ መረጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች አማካኝነት ይሰበሰባሉ፡፡

ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መስክ ምልከታ፣ ሰነድ ፍተሻ እና ቃለ-መጠይቅ ናቸው፡፡

***ሀ. መስክ ምልከታ*** **(Field Observation)፡-** የመስክ ምልከታ የተቀነባበረ በቅድሚያ ለታወቁና ለታቀዱ ጥያቄዎች መልስ ከማግኘት አኳያ የጠለቀ ማሰብንና መመራመርን ተመርኩዞ የሚካሄድ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በየዕለቱ በዘልማድ ከሚካሄደው ምልከታ በጣም የተለየ ነው፡፡ ለጽሑፍና ለቃለ መጠይቅ እንደሚደረገው ሁሉ የመስክ ምልከታ ሪፖርት በጥንቃቄ ተመዝግቦ አጥኚው እንደማስረጃ ሊያቀርበው ይችላል፡፡

ለዚህም ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ መቼት መጠቀም አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ተፈጥሮአዊ ያልሆነ መቼት ተመራማሪው ሁሉንም የሥነ ቃል ዓይነቶች በተፈጥሮአዊ መቼት ብቻ ለመሰብሰብ አይችልም ሲሉ ፈቃደ (1991) ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ከተፈጥሯዊው መቼት ውጪ መጠቀም ግዴታ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተፈጥሯዊ ያልሆነ መቼት ማለት ከአውዱ ውጭ ማንኛውም መረጃ አቀባይ የተገኘበትን ጊዜና ቦታ ተጠቅሞ ተመራማሪው ሥነ ቃል መረጃዎችን የሚሰበስብበት ስልት ነው፡፡ ተፈጥሯዊ ባልሆነ መቼቶች ውስጥ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት ሁኔታዎችን አስመልክቶ ፈቃደ (1991፡123)፣ እንዲህ ይላል፡፡ “አንድ ሰው ከገጠር እስከ ከተማ መጥቶ ለአንድ ተማሪ የለቅሶ ግጥሞች ቢነግረው ወይም አንድ ተመራማሪ እገጠር ትምህርት ቤት ሄዶ እያንዳንዱ ተማሪ የሚያውቀውን እንቆቅልሽ እክፍል ተቀምጦ እንዲፅፍለት ቢጠይቅና ቢፃፍለት፣ እነዚህ ስነቃሎች የተሰበሰቡት ከአውዳቸው ውጭ ነው ማለት ነው” በማለት ፈቃደ (1991፡123) ይገልጻሉ፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ቶክ- ቤኣ በዓል አከባበር ወቅትም በአዲስ ዓመት መግቢያ ላይ የሚካሄድ በመሆኑ ተፈጥሯዊ መቼትን ጠብቆ መረጃ ለመሰብሰብ ጥናቱ የሚካሄድበት ጊዜ አመቺ ባለመሆኑ ተፈጥሯዊ ያልሆነ መቼት በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ምክንያቱም የዚህ ጥናት ዕቅድ እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ ድረስ ሲሆን የቶክ-

ቤኣ በዓል የሚከበርበት ወቅት ደግሞ በአሮጌው ዓመት ማብቂያ እና በአዲሱ ዓመት መባቻ ላይ ነው፡፡

**ለ. ሰነድ ፍተሻ፡-** ሰነድ ፍተሻ መጠቀም የተፈለገበት ምክንያት ስለቶክ-ቤኣ በዓል ክወና ስርዓት በቂ መረጃ ለማግኘት በብሄሩ ተወላጅም ሆነ በሌሎች አካላት ተሰንደው የተቀመጡ መረጃዎችን ለማግኘት ስለሚያመች ነው፡፡

በዚህ መሳሪያ መረጃዎች የተሰበሰበባቸው ቦታዎች በዞኑ ባህል ማዕከል በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ምሁራን ተጽፈው ከተቀመጡ ጽሑፋዊ ሰነዶች፣ እንዲሁም ታትመው ገበያ ላይ ከዋሉ መጽሐፎች፣ መጽሔቶች እና ጋዜጦች ተገቢ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህ የመረጃ ምንጮች ስለበዓሉ አከባበር ክወና ስርዓት እውቀት ያላቸው ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት ሰንደው ያስቀመጧቸው ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡

**ሐ. ቃለ-መጠይቅ፡-** ስለቶክ-ቤኣ በዓል ክወና ስርዓት እውቀት ያላቸውን የተለያዩ ሰዎችና ባለሙያዎችን ቃለ-መጠይቅ በማዘጋጀትና በማቅረብ መረጃ ለማግኘት ይህ ዘዴ አንዱ መንገድ ሆኖ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በሌላኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ወቅት ያልተገኙ መረጃዎችን እና በሰነድ ፍተሻ ወቅት የሚቃኙ ነገር ግን ግልጽነት የሚያስፈልጋቸው እና ማህበረሰቡ ታማኝ መረጃ በቀዳማይ ምንጭነት እንዲያብራሩ የሚፈለጉ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት ነው፡፡ ቃለ መጠይቅን ከሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሚለየዉ ጉዳይ በመላሽና በጠያቂው ሰው መካከል የፊት ለፊት የቃለ ምልልስ መኖሩ ነው፡፡ አለም (2001፣16) ቃለ መጠይቅን ሲገልፁ "ቃለ መጠይቅ ጠያቂ ከተጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝተው በቃለ ምልልስ መረጃ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡" ያለው (2004 ዓ.ም፣178)፡፡ ስለ ቃለ መጠይቅ አጠቃቀም ሲገልጹ "አንድ ተመራማሪ ከዉስን ቃለመጠይቅ (Structured interview)፣ ከፊል ነፃ ቃለ መጠይቅ (Semistructured interview) እና ከነፃ ቃለመጠይቅ (Unstructured interview) ዉስጥ በአንዱ፣ በሁለቱ ወይም በሦስቱም መጠቀም ይችላል" ባሉት መሰረት መረጃውን ከመረጃ አቀባዮች መሰብሰብ ይቻል ዘንድ ቃለ መጠይቁ በሁለት መንገድ የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው መረጃ አቀባዮችን ከመጠየቄና ከማግኘቴ በፊት ቀድሜ ዉስን ቃለመጠይቅ አዘጋጅቻለሁ፡፡ ይህም ሰፋ ያለ ውይይት ለማድረግ የሚያስችል ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር ተገናኝቼ ቃለመጠይቅ በማደርግላቸው ወቅት ከማያቸውና ከምሰማቸው መረጃዎች በመነሳት ለምን? እንዴት? ከዚያስ? ወዘተ በማለት ለመጠየቅ፣ ተጠያቂዎችም እንዲሁ በነፃነት መልስ ይሆናል ብለዉ የሚገምቱትን እና ያመኑትን መረጃ የሚሰጡበት ነፃ ቃለመጠይቅ አካሂጃለሁ፡፡

## 3.5. የመረጃ አደረጃጀት

የጥናቱ ዋና ዓላማ የዳውሮ ብሔረሰብ ቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል ክወና ስርዓትን መተነተን ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት መስክ ምልከታ፣ ሰነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ መረጃ የተሰበሰብባቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በመስክ ምልከታ፣ በሰነድ ፍተሻ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በዓይነት በዓይነት የመለየትና የማደራጀት ሥራ ተሰርቷል፡፡ በመቀጠልም የቀረቡት መረጃዎች ትክክለኛነታቸውና አስተማማኝነታቸው ተፈትሿል፡፡ በመጨረሻም በዚህ መልክ የተደራጁ መረጃዎች ቀጥሎ በቀረበው መንገድ ለትንተና ቀርበዋል፡፡

## 3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ መተንተኛ ዘዴ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህን ጥናታዊ ፅሑፍ ለማካሄድ ስለቶክ-ቤኣ ተፅፎ የሚገኙ የተለያዩ ፅሑፎችን በጥልቀት በማንበብ፣ እንዲሁም ቃለ-መጠይቁ ከቀረበላቸው ሰዎች መረጃውን በቁጥር ሳይሆን በፅሑፍ የሚተበሰበ ሲሆን በጽሑፍ የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን ስለሚያስችል ነው፡፡ ምንም እንኳ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ የተለያዩ የመተንተኛ ስልቶችን ያካተተ ቢሆንም ለዚህ ጥናት ተግባር ላይ የዋለው ዘዴ ገላጭ ተንታኝ የመተንተኛ ዘዴ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት፤ መረጃ ትንተና

## 4.1. የመረጃ ትንተና

ቀደም ባሉት ሦስት ምዕራፎች የጥናቱ መግቢያ፣ ክለሳ ድርሳናት እና የጥናቱ ዘዴ ቀርበዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የዳውሮ ብሔር አዲስ ዓመት (ቶክ-ቤኣ) ትርጉም፣ በዓል አከባበር፣ በዓሉ የሚከበርበት ቀን፣ ለበዓሉ የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች፣ የበዓሉ አከባበር ሂደት፣ ከበዓሉ ጋር በተያያዘ የሚከወኑ ባህላዊ ክዋኔዎች፣ እንዲሁም በበዓሉ ወቅት የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦች ዓይነትና አዘገጃጀት ተተንትኖ ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1. የዳውሮ ብሔር (Tokki Be’aa) ዘመን መለወጫ ትርጉም

ስለቶክ-ቤኣ ትርጉም ማብራሪያ እንዲሰጡ ከተጠየቁት መረጃ ሰጪዎች መካከል ኢራሻ ደስታ (የአካባቢው ባላባት)፣ አቶ ታዬ (የዞን ባህል ቱሪዝም ባለሙያ እና የብሔሩ ተወላጅ) እንዲሁም ወይዘሮ አዲሴ (የዞን ባህል ቱሪዝም ባለሙያ እና የብሔሩ ተወላጅ) በተመሳሳይ ሲገልጹ የሚከተለውን ይላሉ፡፡ "ቶክ-ቤኣ ማለት ጥሬ ትርጉም ተሸክሞ ማየት ወይም መዝኖ ማየት እንደ ማለት ሲሆን በበዓሉ ዋዜማ ዕለት ምሽት በቤቱ ያለ ሰውም ሆነ እንስሳ ጠግቦ ካልበላ እና በሸክም ሲመዘን ቀለል ካለ አዲሱ ዓመት የጥጋብ ዓመት ላይሆንለት ይችላል የሚለውን መልዕክት የያዘ ቃል ነው፡፡ የዘመን መለወጫ በዓል ዋዜማ ዕለት ቶክ-ቤኣ ሲባል የበዓሉ ማግስት ላይታ ላሚያ (hinggic’c’aa) ተብሎ ይጠራል ትርጉሙም የደስታ በዓል ማለት ነው፡፡ ላይታ ላሚያ (Laytsa laamiya) የቶኪ-ቤኣ ማግስት ስሆን ጥሬ ፍቺዉ ዓመት መለወጫ እንደ ማለት ነዉ፡፡

ላይታ-ላሚያ (Laytsa laamiya) በዳዉሮ ብሄር ሁሉም ሰዉ በዋዜማዉ ዕለት /ቶክ-ቤዓ/ ጠግቦ አድረዉ የሚቀበሉት የአዲስ ዓመት በዓል ነዉ፡፡" በማለት ያብራራሉ፡፡ የዘመን መለወጫ (Laytsa laamiya) በዳውሮ አቆጣጠር (Dawuro payduwa wogaa) የጨረቃ መውጣትና መግባትን መሠረት ያደረገ የቀን አቆጣጠር ሲሆን የጨረቃ ይዘት፣ ቅርጽና መልክ እንዲሁም የመውጫ ሰዓት መቀያየርን ተከትሎ ጊዜን የመቁጠርና የመተንበይ ጥበብን ያካትታል፡፡" በማለት ስለትርጉሙ ያስረዳሉ፡፡

"የዳውሮ ብሄረሰብ የዘመን መለወጫ በዓል (ቶክ- ቤኣ) የብሄረሰቡ ባህላዊ የምግብ ዝግጅቶች የሚተዋወቁበት፣ የሙዚቃ፣ ድራማና ትውን ጥበባት የሚናስተዋወቅበት፣

ባህላዊ ዳኝነት እና የግጭት አፈታት የሚካሄድበት እና እርቀሰላም የሚወርድበት ለብሄረሰቡ የቋንቋ ልማት ቀረርቶ፣ ፉከራ፣ ሽለላ፣ እንጉርጉሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍበት ከባእድ አምልኮ የራቀ የባህል መድረክ ነው፡፡

ቶክ-ቤኣን ከሌሎች አዲስ ዓመት በዓላት ጋር የሚያስተሳስራቸው ነገር ምን አለ ለሚል ቃለ መጠይቅ ማብራሪያ የሰጡ መረጃ ሰጪ አቶ ታዬ (የዞን ባህል ቱሪዝም ባለሙያ እና የብሔሩ ተወላጅ) እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ በእርግጥ የቶክ-ቤኣ ዘመን አቆጣጠር የጨረቃን መውጣት መሠረት ያደረገ ጥበብ ቢሆንም እንኳ ልክ እንደ አብዛኞች ሀገራት አዲስ ዓመት በዓላት በአሮጌ ዓመት መጨረሻ እና በአዲስ ዓመት መባቻ ላይ የሚከበር መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቶክ-ቤኣ (የዳውሮ አዲስ ዓመት) ልክ እንደ ሌሎች አዲስ ዓመት 365/366 ቀናትን አሳልፎ በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ቀን የሚቀበሉት መሆኑ ከሌሎች ሀገራት አዲስ ዓመት ጋር ያመሳስለዋል ይላሉ፡፡ ደግሞም ቶክ-ቤኣ ልክ እንደ ሌሎች የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አዲስ ዓመት በዓሎች አሮጌውን ዓመት ያሻገራቸውን አምላክ በማመስገንና አዲሱን ዓመት እንዲባርክላቸው በጸሎት የሚከበር መሆኑ ሌላው የሚያመሳስለው ጉዳይ ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ሌላኛው ስለቶክ-ቤኣ በዓል ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ እንደሚያስረዳው ቶክ-ቤኣ በዳውሮ ብሔረሰብ ዘንድ የዘመን መለወጫ በዓል በመባል የሚታወቅ ሲሆን በዓሉ የጨረቃ አወጣጥን መሠረት በማድረግ የቀናትና የወራት አቆጣጠር ድምር ውጤት ነው፡፡

እንደ ዩኒክ ኢትዮጵያ (2008፣30) ገለጻ ከዚህም የተነሳ በአንድ ዓመት ውስጥ አስራ ሁለት ወራት ሲኖሩ (Mask'k'alaa) መስከረም፣ (S'ik'inttiya) ጥቅምት፣ (Hidaariya) ህዳር፣ (Taysaasiya) ታህሳስ፣ (Ichecheshiya) ጥር፣ (Usuppuniya) የካቲት፣ (Laappuniya) መጋቢት፣ (Hosppuniya) ሚያዚያ፣ (Udduppuniya) ግንቦት፣ (Tammiya) ሰኔ፣ (Hamiliya) ሐምሌ፣ (Naasiya) ነሐሴ እና K'aak'umiya ጳጉሜ ተብለው እንደ ቅደም ተከተላቸው ይጠራሉ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በዳውሮ ብሔር የቀን አቆጣጠር መሠረት አንድ ዓመት በአራት ወቅቶች ተከፋፍሎ ይቀመጣል፡፡ ከመስከረም እስከ ጥቅምት ድረስ ያለው አድሊያ (Adilliya woy Ofintsaa)፣ ከህዳር እስከ የካቲት በጋ (Boniya)፣ ከመጋቢት እስከ

ግንበት አሱራ (Assuuraa)፣ ከሰኔ እስከ ጳጉሜ ድረስ ክረምት (Balgguwa) ይባላሉ፡፡

አዲሊያ (Adilliya woy Ofintsaa) ማለት አደይ አበባ የሚያብብበት ወቅት በመሆኑ ስያሜው ከዚያ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በኃ (Boniya) ማለት ጸሐይ የሚበረታበት ዛፎች ቅጠላቸውን የሚያራግፉበትና ሳር የሚደርቅበት ወቅት ማለት ነው፡፡ ሌላኛው አሱራ (Assuuraa) ሲሆን ይህም ማለት የበልግ ወቅት ሆኖ አንዳንድ ዛፎችና ሳሮች የሚበቅሉበት እንዲሁም ለተለያዩ የእርሻ ሥራዎች መሬት የሚታረስበትና የአገዳ እህሎች የሚዘሩበት ወቅት ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ወቅት ሰዎች የሚበሉት ነገር እጥረት የሚያጋጥምበት ወቅት ነው፡፡ ከሰኔ እስከ ጳጉሜ ክረምት (Balgguwa) ሲሆን የዝናብ ወቅት በመሆኑ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ለተጠቀሱ ወቅቶች የተሰጡ ትርጉሞች ከዓመቱ የአየር ሁኔታ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ መቼም ስለዘመን አቆጣጠር ስናነሳ በዓመት ውሰጥ ስለተከታታይ ወራት ገለጻ መስጠታችን አይቀሬ ነው፡፡ በመሆኑም የዳውሮ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የጊዜ አቆጣጠር ባለቤት እንደመሆኑ አንድ ቀን ከንጋት እስከ ንጋት ያለውን ጊዜ የሚያጠቃልል ሲሆን በተለያዩ ጊዜያትም የተከፋፈለ ነው፡፡ እነሱም፡- (Guurraa) ንጋት፣ (Wonttaa) ጥዋት፣ (Gallassaa) ረፋድ፣ (Awa kawutuwa) ቀትር፣ (Awa doshuwa) ከሰዓት፣ (Awa wulaa) ጸሐይ ግባት፣ (Omarssaa) ማምሻ፣ (K'ammaa) ማታ፣ (Bilahiya) ሌሊት፣ (Hekka bilahiya) እኩለ ሌሊት፣ (Wonttumaatsaa) ሊነጋጋ ሲል በመባል ይታወቃል፡፡

ሌላው ዩኒክ ኢትዮጵያ (2008፣30) ከዳውሮ ዘመን አቆጣጠር ጋር አያይዞ ስለ "ጨገና" (C'eggennaa) የሚከተለውን ያብራራል፡፡ "ጨገና" (C'eggennaa) ማለት በወራት ውስጥ ያሉ መጥፎ ቀናት የሚባሉት ሲሆኑ በእነዚህ ቀናት የቤት መስሪያ ዛፍ የማይቆረጥበት፣ የተለያዩ የእህል አይነቶች የማይዘሩበት፣ የተዘሩትም ቢሆኑ የማይታጨዱበት እንዲያውም የማታረሙበት እንደው በአጠቃላይ የማይነኩበት ጊዜ ነው፡፡ ምክንያቱም በእነዚህ ቀናት ዛፍም ሆኑ የአገዳ እህሎች ከተቆረጡ ወይንም ከተነኩ ስለሚነቅዙ ወይም ስለሚደርቁ ተብሎ ይታመናል፡፡

ጨረቃ በወጣች በአምስተኛው ሳምንት ጠፍታ ዳግመኛ ልትወጣ አንድ ቀን በፊት ንጋትም ሆነ ማታ ሳትታይ የቀረችበት ቀንና በከብት ቀንድ ቅርጽ ከታየች ከአስራ አምስት ቀን በፊት ያሉት አምስት ቀናት ጨምሮ "ጨገና" (C'eggennaa) ተብለው

ይጠራሉ። ማለትም ጨረቃ ጠፍታ ከተገኘች በኋላ ሁለተኛ ጊዜ ከመጥፋቷ በፊት ያለው አንድ ቀንና በቀንድ ከብት ቅርጽ ከታየች ከ11ኛው ቀን እስከ 15ኛው ቀን ድረስ ያሉት አምስት ቀናት ማለት ነው።



ምስል ሁለት፡- በቶክ-ቤኣ በዓል ዕለት የምግብ ዕቃዎች ለበዓሉ በተዘጋጁ ምግቦች የተሞሉበትን የሚያሳይ፤

## 4.1.2. ቶክ-ቤኣ በዓል መቼ ይከበራል?

በዳውሮ ብሔረሰብ ዘንድ ቶክ-ቤኣ መቼ እንደሚከበር መረጃ እንዲሰጡኝ ከጠየኳቸው የመረጃ ምንጮቼ አቶ ታዬ እና ወይዘሪት ስንቅነሽ (የዞን ባህል ቱሪዝም ባለሙያ እና የብሔሩ ተወላጅ) የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል። የዳውሮ ብሔር ከጥንት ጀምሮ የነበረ የጨረቃ እንቅስቃሴን እየተከታተሉ የቀን አቆጣጠር /lunar calendar/ አለው። ይህም ኦማቲያ ፓይዱዋ /የዳውሮ አቆጣጠር/ ይባላል። ቶክ-በኣ ከጥንት ጀምሮ በብሔረሰቡ ዘንድ የክረምት ወራት ማብቂያና የፀደይ ወራት መቀበያ፣ የክረምቱ ጥቁር ሰማይ ወገግ ብሎ መስኩ ቡቃያ ለብሶ፣ በሰላም ላከረመው አምላክ ምስጋና የሚቀርብበትና መጪው ጊዜ ከቤተሰብ እስከ ሀገር የሰላም፣ የጤና፣ የጥጋብ እንዲሆን በመመኘት፣ በጋራ በመሆን፣ ከየአይነቱ ምግብ ተዘጋጅቶ በታላቅ ደስታ የሚከበር የብሄሩ የቆየ ባህላዊ እሴት ነው።

በዳዉሮ ባህል በአሮጌ ዓመት መባቻና በአዲስ አመት ዋዜማ፣ ወይም ከነሐሴ ወር ጨረቃ መጨረሻ እስከ መስከረም ወር ጨረቃ መግቢያ (መታያ) ቀን ድረስ ያሉት

ተከታታይ አምስት /ስድስት/ ቀናት የቶክ-ቤኣ ቀናት ተብለው ይወሰዳል በማለት መብራቱ (የዞን ባህል ቱሪዝም ባለሙያ) በተጨማሪ የሚያብራሩ ሲሆን ዩኒክ ኢትዮጵያ (2008፣31) ይህንኑን ያረጋግጣል፡፡

"ቶክ-ቤኣ" በዳውሮ ማህበረሰብ መካከል ዝናባማ ወቅት መጨረሻ ላይ ክረምትና ፀሐያማ፣ ብሩህ ወቅት፣ በጋ ከጥንት ጀምሮ በጳጉሜን ወር የሚከበር በዓል ነው፡፡ ህብረተሰቡ እግዚአብሔር የሰጣቸውን በረከቶች ሁሉ በመቁጠር የሚያከብረው ጊዜ ነው፡፡ በሰላም እንዲቆዩ ስለፈቀደላቸው ምስጋናቸውን የሚያቀርቡበት ወቅትም ነው፡፡ መጪው አመት ሰላምን፣ ፍቅርን፣ ብልጽግናን ከቤተሰብ ወደ ሀገሩ ሁሉ እንዲያወርድ ይጸልያሉ፡፡ በዓሉም ከዚሁ መንፈስ ጋር በመሆን ችቦ በማብራት፣ በመብላትና በመጠጣት፣ በደስታ በመነጋገር በድምቀት እና በታላቅ ደስታ ይከበራል፡፡

በዳውሮ ብሔረሰብ ቀን አቆጣጠር በስተግራ (ሃድርሳ ባጋን) ጨረቃ ለመጀመሪያ ጊዜ በስተምዕራብ ስትገኝ አዲሱ ወር ገባ ይባላል፡፡

አዲስ ጨረቃ በመጀመሪያ ስትወጣ በጥቂት ሰዎች ዓይን የምትታይ ሲሆን ይህም በዳውርኛ ‹‹miya kac'iyan beettaaddu›› ወይም ጨረቃ በከብት ቀንድ ታየች ይባላል፡፡ ጨረቃ ወጥታ በሁለም ሰው ዓይን ስትታይ ‹‹agenatta s'eeraaddu›› /ጨረቃ ወጣች/ ይባላል፡፡ ስለዚህ ጨረቃ በከብት ቀንድ የታየችበትን ቀን የወሩ መጀመሪያ ቀን ሲሆን ወጥታ በብዙ ሰው ዓይን የታየችበት ቀን የወሩ ሁለተኛ ቀን ይሆናል፡፡ በመጀመሪያ ስትወጣ በጣም ቀጭንና ደጋን ቅርጽ የነበራት ጨረቃ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረች ሄዳ በከብት ቀንድ (miya kac,iyan) ከታየችበት በ15ኛው ቀን ወደ ሙሉ ክብ ቅርጽ ተቀይራ ስትወጣ በጣም ቀልታና በይዘትም የመጨረሻውን ሥፍራ ትይዛለች፡፡ ይህም ክስተት በዳውሮኛ ዶይሱዋ /doysuwa/ ወይም አገናታ ዶይሳደ /agenatta doyssaaddu/ ይባላል ማለትም ሙሉ ጨረቃ ታየ እንደ ማለት ነው፡፡

ዶይሱዋ አንድ ቀን ሲቀር (ከወጣች 14ኛው ቀን ማለት ነው) ጨረቃ በከፊል ትቀላለች በቅርጽም ወደ ሙሉ ክብነት ትጠጋለች፡፡ ይህ ሁኔታ በዳውሮኛ ‹‹Agenatta lap'addu›› ይባላል፡፡ ጨረቃ በመጠን እያነሰች ሄዳ አንድ ቀን ብቻ ከሰው ዓይን ጠፍታ የምታድርበት ቀን የወሩ መጨረሻ ቀን ሲሆን ከዶይሱዋ በኋላ 13 ቀን ቆይታ ትጠፋለች፡፡

በዳውሮ የቀን አቆጣጠር መሰረት አንድ ወር 28 ቀናት ያሉት ሲሆን አንድ ዓመት ደግሞ 12 ወራት አሉት፤ ምክንያት ጨረቃ በዓመት ሁለት ጊዜ ደጋግሞ ከበስተምእራብ (Wulaha) በኩል ስለምትወጣ ነው።

የአዲሱን ጨረቃ መውጣት ሁሉም ሰዎች ማወቅ ይችላሉ ወይ ተብለው የተጠየቁት መረጃ ሰጪዬ አቶ ዱባ ላሞሬ አዲስ ጨረቃ በመጀመሪያ ስትወጣ በቀን አቆጣጠር ዕውቀታቸው ልዩ ጥበብ ካላቸው አዋቂዎች በስተቀር ሁሉም ሰዎች አዲሷን ጨረቃ ሊመለከቷት አይችሉም። ቀኑን በትክክል መቁጠር የሚችል ሰው አዲስ ጨረቃ መውጣቷን የሚረዳው ማታ ከብት በሚገባበት ሰዓት የሰማይ ወገግታ በማየት አዲስ ጨረቃ መውጣቷን በማስተዋል ነው በማለት ያብራራሉ።

እንደ አጠቃላይ ቶክ-ቤኣ እንደሰከረ ሰው አይን የደፈረሰ ውሃ ኩልል ብሎ በሚጠራበት፣ በደመና ተሸፍኖ የጠቆረው ሰማይ በተለይም ድቅድቁና ጭጋጋማው የሐምሌ ጨለማ በጨረቃ ብርሃን በሚደምቅበት፣ ብርዳማው ክረምት አልፎ ጸሐይ ጮራዋን በምትፈነጥቅበት፣ አበቦች በሚፈኩበት፣ በነሐሴ መገባደጃ፣ በመስከረም መባቻ የሚከበር ከተፈጥሮ የተሳሰረ የዘመን መለወጫ በዓል ነው በማለት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መረጃ ሰጪዎች በዓሉ ስለሚከበርበት ጊዜ ይገልጻሉ።

የዳዉሮ ብሔረሰብ የዘመን አቆጣጠር አገር በቀል ዕዉቀታቸዉን ለማስረዳት የጨረቃን እንቅስቃሴ መሠረት እንደሚያደርግ አቶ ታዬ እና ኢራሻ ደስታ እንደሚከተለዉ ይገልፃሉ።

- Agenatta miyaakac’iyaan beetaaddu፡- አመሻሽ ላይ ከብቶች ወደ ቤት በሚገቡበት ጊዜ የሰማዩን ወገግታ በማየት ጨረቃ በከብት ቀንድ ቅርጽ ታየች ማለት ነው። ትንሽ ጨረቃ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ብላ ስትታይ ባህላዊ የክወክብት ቆጠራ ዕዉቀት ባላቸዉ ዉስን ሰዎች ካልሆነ በስተቀር በሁሉም ሰዉ ዓይን አትታይም። አዲስ ጨረቃ ስትወጣ በስተምዕራብ በኩል ትታያለች። ይህ ቀን በዳዉሮ የዘመን ቀመር የወሩ የመጀመሪያ ቀን ነዉ ሲሉ ይገልጻሉ።
- Agenatta S’eeraddu፡- የወሩ ሁለተኛው ቀን ጨረቃ በከብት ቀንድ ከታየችበት ቀን ቀጥሎ ያለ ሁለተኛው ዕለት ሲሆን ጨረቃ በሁሉም ሰው ዘንድ መታየት የምትጀመርበት ቀን ነዉ ይላሉ።

- Agenatta Lap'aaddu፡- ከወሩ አጋማሽ አንድ ቀን ቀደም ተብሎ፣ የወሩ አጋማሽ ዋዜማ፣ ጨረቃዋ የወጣችበት 14ኛው ቀን መሆኑን የሚያሳይ ነዉ።
- Agenatta Doyssaaddu፡- የወሩ አጋማሽ መድረሱን ማመላከቻ፣ ጨረቃ በወጣችበት 15ኛዉ ቀን፣ ሙሉ በሙሉ ክብ ሆና የሚትታይበት ቀን ነዉ በማለት ይገልጻሉ።
- C'eggenna፡- ጨረቃዋ በምትወጣበት ከ1-3 ያሉትን እኩይ ቀናትና መጨረሻ ላይ ጨረቃ እስከምትጠልቅበት ድረስ ያሉ ከ25-28 ያሉ እኩይ ቀናት የሚያጠቃልል ነዉ። የጬገና ቀናት እኩይ የተባሉበት ምክንያት ለምንድነው ስል ላቀረብኩላቸው ጥያቄ በእነዚህ ቀናት ለግንባታ ሥራ እንጨት ቢቆረጥ ጥንጣን ይበላዋል፤ ምርት ከማሳ ቢሰበሰብ ነቀዝ ይበላዋል፤ በጬገና ወቅት እንስሳት ቢያረግዙ ጥሩ ጥጃ አይወለድም፤ ሌላዉ ቀርቶ በእነዚህ ቀናት ሴቶች ቢያረግዙ እንኳን ልፍስፍስ ልጅ ይወለዳል ይላሉ። እንደ መረጃ ሰጪዎች ገለጻ ከሆነ በአንድ ወር ዉስጥ በአማካይ 6 (ስድስት) የጬገና ቀናት እንዳሉ ያስረዳሉ።
- Poo'o C'eggenna፡- በወሩ መጀመሪያ ጨረቃዋ ከታየችበት የመጀመሪያ ቀን እስከ 3 ቀናት ያለ እኩይ ጊዜ አመላካች ቀናት ማሳያ ነዉ ሲሉ ይገልጻሉ።
- D'uma C'eggenna፡- እንደ መረጃ ሰጪዎች ገለጻ ጨረቃዋ ልትጠልቅ 3 ቀን ሲቀራት ጀምሮ እስከሚቀጥለዉ ጨረቃ መዉጫ ቀን ድረስ ያሉ እኩይ ቀናት ናቸዉ።

### 4.1.3. የቶክ-ቤኣ በዓል ቅድመ ዝግጅቶች

በዳውሮ ብሔረሰብ ለቶክ-በዓል ምን ምን ቅድመ ዝግጅቶች እንደሚደረጉ መረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁ አቶ ዱባ ላሞሬ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ።

"በቶክ-ቤኣ በዓል ቀን ድመትና ውሻውን ጨምሮ የቤት እንስሳት ጠግበው መብላት ይጠበቅባቸዋል። ለከብቶች ሳር በበቂ ሁኔታ ይታጨድላቸዋል። ምክንያቱም ጠግቦ ያልበላውን በዚያን ሌሊት የአሮጌው አመት መንፈስ ተሸክሞ አይቶት ከቀለለው ይዞት ይሄዳል፤ ከጠገበ ስለሚከብደው አይሞክረውም ተብሎ ይታመናል።" ይላሉ።

በተጨማሪም አቶ ታዬ በቤት ውስጥ ያሉ የዕህል ማስቀመጫ፣ የወተትና ውሃ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችም ባዶ እንዳይሆኑ ይደረጋል። ምክንያቱም በዕለቱ ያልጠገበ አመቱን ሙሉ ረሃብተኛ ይሆናል። ሙሉ ያልሆኑ ነገሮች ዓመቱን ሙሉ ጉድለት ያሳያሉ፣ከቤት ውጪ ያደረ ዓመቱን በሙሉ ውጪ ይቀራል፣ የማይታረቅ በአድሱ

አመት ጥሩ ነገር እንደማይገጥማውና እንደተጣላ ይከርማል ተብሎ ስለሚታመን ነው በማለት ያብራራሉ። ስለሆነም ሰውም ሆነ እንስሳት ጠግቦ ማደር ይኖርባቸዋል፤ ቤት ውስጥ ያሉ ሁሉም የእህል እቃዎች መሞላት አለባቸው ይላሉ።

ቶክ-ቤኣ በአዲስ አመት ባህሉና ስርዓቱ እንዲሁም የሀገር ክብሩ የተጠበቀለት እንዲሆን ምርት እንዲጨምር፣ በሽታና መቅሰፍት ፣ጦርነት ረሃብ ውዘተ እንዳይከሰት፣ መልካሙን ሁሉ ለሀገሩና ለህዝቡ በመመኘት ፈጣሪን እየለመኑ የሚያከብሩት የዘመን መለወጫ ስርዓት ነው።

የቶክቤዓ በዓል ከመድረሱ በፊት በሴቶችም ሆነ ወንዶች ሀብታምም ሆነ ድሃ እንደየአቅሙ ለበዓሉ አስፈላጊውን ዝግጅቶችን ሁሉ ያደርጋሉ። ለባጭራና ለቂጣ የሚሆን እንሰት ተፍቆ ይዘጋጃል፤ ለቦርዴ ጤላ የሚሆን እህል ተፈጭቶ ኦካታ በቅጠል ታስሮ ይቀመጣል፣ የተለያዩ እህል ዓይነቶች ይፈጫል፣ ቅመማቅመም ይዘጋጃሉ፣ እቤት የወተት ላሞች ካሉ የበዓል ቅቤና አይብ ይጠራቀማል፣ እቤት ወተት ከሌለ በግዥ ለማግኘት ለበዓሉ 15 ቀንና ከዚያ በላይ ጊዜ እያለ ከባለወተቱ ጋር ቀጠሮ ይያያዛል። የቦርዴ ጠላ ዝግጅት ይደረጋል። ሀብት ያላቸው የእርድ ከብትም በየበኩሉ እየተዘጋጀ ይቆይና ለበዓሉ ሦስት እስከ አምስት ቀናት ሲቀሩ ሴቶች ለበዓሉ ጊዜ የሚሆን ቆጮ ይቆርጣሉ።

በተለይ በቶክ- ቤኣ በዓል ጊዜ አይቀረው ክዋኔ ልጃገረዶች የእጅ ጥፍሮቻቸውን ለማስዋብ የሚያደርጉት ክዋኔ ነው። ልጃገረዶች ጥፍሮቻቸውን ለማስዋብ የሚሆን እንሶስላ (Wosolluwa) ከጫካ ቆፍረው በማምጣት አጥበውና ፍቀው ያዘጋጃሉ፣ የቆላማው አከባቢዎች ከደጋማው አካበቢ በግዢ ወይም በስጦታ አገኝተው ያዘጋጃሉ። ይህንን ያገኙትን እንሶስላ (Wosolluwa) ድጠው ካዘጋጁ በኂላ በዋዜማው እለት ምሽት በሁለቱም እጅ ጣቶቻቸው እርስበርስ በተለበለበው ለጋ ቅጠል ጠቅልለው ያሳድራሉ።

በተጨማሪም የመኖሪያ ቤት ደጃፍና ዙሪያ ያስተካክላሉ ወይም ያፀዳሉ፤ ወንድ ልጆችም በበዓሉ ቀን ያለምንም ሥራ እየተጫወቱ ለመዋል ብለው የማገዶ እንጨትና የከብት ሣር ከበዓሉ በፊት ሁለት ወይም ሦስት ቀን እያለ የሰፈር ልጆች በቡድን በመሆን ለሁሉም ቤት ይሰበስባሉ።

የቶክ-ቤኣ በዓል ከመድረሱ በፊት ሴቶችም ሆኑ ወንዶች፣ ሀብታምም ሆነ ድሃ እንደየአቅሙ ለበዓሉ አስፈላጊ ዝግጅቶችን ሁሉ ያደርጋል፡፡ እንስት ተፍቆ ይዘጋጃል፣ ለቦርዴ እና ጠላ (ገሾ ፓሪሷ) የሚሆን እህል ተፈጭቶ ኡኩታ (ukitsaa) ይዘጋጃል፣ ቅመማቅመም ይዘጋጃል፣ እቤት የወተት ላሞች ካሉ የበዓሉ ቅቤና አይብ ይጠራቀማል፣ እቤት ከሌሉ በግዢ ለማግኘት ከበዓሉ ከአንድ ወር ቀድሞ ከባለወተት ጋር ቀጠሮ (keeruwa) ይያያዛሉ፤ የዕርድ ከብትም እንዳስፈላጊነቱ ካለበት ተፈልጎ ይገዛል፡፡ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ሁሉም ለበዓሉ በየበኩሉ እየተዘጋጀ ይቆይና ለበዓሉ ሁለት ወይም ሦስት ቀናት ሲቀሩ ሴቶች ለበዓሉ የሚሆን ቆጮ ይቆርጣሉ፣ በተጨማሪም የመኖሪያ ቤት ደጃፍና ዙሪያ ያስተካክላሉ ወይም ያጸዳሉ በማለትም አቶ ዱባ ላሞሬ ይገልጻሉ፡፡

### 4.1.4. ለ"Tookki Be’a" በዓል የህብረተሰብ እና የቤተሰብ አባላት ድርሻ

የዳዉሮ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ (Tookki Be’a) በዓል አከባበር ወቅት የተለያዩ የቤተሰብ አባላትና የህብረተሰብ ክፍሎች ምን ሃላፊነት እንዳላቸው እንዲያብራሩ ወይዘሮ አዲሴ እና አቶ ዘርሁን የዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያዎችና የብሔሩ ተወላጆች እንዲሁም አቶ ዶግሶ በተመሳሳይ የሚከተለውን ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡

- **አባት:-** ለበዓሉ እህል እና ሥጋ ፣ … ወዘተ ማቅረብ፣ የዓመቱ መጨረሻ ዕለት በአዲሱ አመት ዋዜማ ምሽት **ጉጠት** (S’iifaa) ይዞ በጉጠት ጫፍ ላይ ትንሽ ስጋ በማኖር ወይም ደግሞ ቅቤ በመቀባት ቤት ውስጥ እየዞረ እርሀብ፣ በሽታ፣ ድርቅ፣ ቸነፈር ከቤቱና ከአገር እንዲወጣ፣ መጪዉ አዲሱ ዓመት የጥጋብ፣ የደስታ፣ ዓመት እንዲሆን ፈጣሪ እየለመነ ወደ ውጪ ይወረውራል፡፡
- **እናት:-** ለበዓሉ የሚሆን ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች የሚሆኑ ጥሬ እቃዎችን አስቀድመዉ ያሰባስባሉ፤ በዕለቱ ለቤተሰቡ የሚሆን ባህላዊ ምግቦችን ያዘጋጃሉ፡፡
- **ወንድ ልጆች:-** እንጨት መልቀም፣ ከብቶች ጠግበው በልተው እንዲያድሩ ሣር ማጨድ፣ ወዘተ ተግባራትን ለበዓሉ ስኬት አስቀድመዉ ያሟላሉ፡፡ ተሰባስበው ሂዮ ባሎ ወይም ባላ ሂዮ እያሉ እየዘፈኑ ይጨፍራሉ፡፡
- **ሴት ልጆች:-** እናቶችን ጓዳ ዉስጥ መርዳት፣ውሃ መቅዳት፣ ለራሳቸዉ እንሶስላ (wosolluwa) ከጫካ ቆፍረው በማምጣት በድንጋይ ወፍጮ ድጠው እጃቸዉንና እግራቸዉን መኳኳል ከዚያ ከጥዋት እስከ እኩለ ቀን በመንደሩ ውስጥ እየዞሩ አንዶስ ዮያ ወይም ወራታይ ወስከ እያሉ እየዘፈኑ ይጨፍራሉ፡፡

- **ጎረቤቶች፡-** በየቤቱ ተራ በተራ እየዞሩ የእንኳን አደረሳችሁ በመመራረቅ በጋራ ተሰባስበው ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ በእንዲህ ያለ ሁኔታ የዳዉሮ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ ቶኪ ቤዓ በዓል የባህል ዝግጅት እስከ ሳምንት ድረስ ጎረቤታሞች አንደነታቸዉን በማጠናከር፣ ያላቸዉን አካፍለው እየበሉና እየጠጡ በደማቅ ሁኔታ ያከብራሉ፡፡
- **ሽማግሌዎች፡-** በበዓሉ ዋዜማ ሳምንት የተጣሉትን ያስታርቃሉ፣ በበዓሉ ዕለት ሕዝቦችን ይመርቃሉ፣ አገሩን ይባርካሉ፣ በአዲሱ ዓመት ዝናብ እንዲዘንብ፣ አዝመራ ምርት እዲሰጥ፣ ልጅ እንዲወለድና ለቁምነገር እንዲበቃ፣ ላም እንድትወልድና ወተት እንድትሰጥ፣ ጥጃዉ አድጎ የሚያንራ በሬ እንዲሆን፣ ወንድ ልጅ እንዲወለድ፣ ጎረቤት፣ ሰፈር፣ ሕዝብ፣ አገርና መንግስት ሰላም እንዲሆን ያላቸዉን በጎ ምኞት በመግለፅ ከሶስት ጎሣ አበላት የተመረጡ አዛዉንቶች ተራ በተራ ሲመርቁ ሕዝቡ ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ከአንገቱ አጎንብሶ በመቆም አሜን እያለ ምርቃቱን ይቀበላል፡፡ በማለት ያብራራሉ፡፡

### 4.1.5. ለቶክ-ቤኣ በዓል የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች

በዳውሮ ባህል በቶክ-ቤኣ ጠግቦ በልቶ የማያድር ሰው ይመዘናል የሚል አንድምታ ስላለ አቅም የፈቀደውንና ቤት ያፈራውን የተለያዩ የምግብ ዓነቶች አዘጋጅቶ ጠግቦ በልቶ የተረፈውን በተለያዩ የምግብ ዕቃዎች ሞልቶ ማሳደር በብሔረሰቡ የተለመደ ተግባር ስሆን እንደየቤተሰቡ አቅም የተለያዩ ምግቦች ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህ ምግቦች በዋናነት ምን ምን ናቸው?፣ ከምን ከምን ይዘጋጃሉ?፣ እንዴት ይዘጋጃሉ? ለሚል ጥያቄ መረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁት ወይዘሮ አጸዴ፣ ወይዘሮ ፋልታም እና ወይዘሮ አዲሴ ዘለቀ በተመሳሳይ ሲገልጹ በቶክ-ቤኣ በዓል ቀን የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦች አብዛኛውን ከእንሰት፣ ከእንስሳት ተዋጽኦ፣ ከስራስሮች፣ እንዲሁም ከሰብል ዓይነቶች በተለያየ መልክ የሚሠሩ ናቸው፡፡

ከዚህም መካከል በዋናነት የሚታወቁት፡- ባጭራ፣ ኡታ፣ ሲሊሏ፣ ታንጨዋ፣ ጎመን በቅቤ (ቡሊያ)፣ ሼሊያ... ወዘተ ሲሆን እነዚህ በማባያነት የሚቀርቡ ሲሆን ከእነዚህ ማባያዎች ጋር የሚቀርቡ የቆጮ፣ የጤፍ፣ የማሽላ፣ የበቆሎ ቂጣዎች፣ የእሸት በቆሎ ቂጣ (ሣሌከታ) እና የበቆሎ፣ የጤፍ፣ የአጃ "ቦሩዋ" ናቸው፡፡

በቶክ-ቤኣ በዓል ጊዜ ስለሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦች አዘገጃጀትና አሠራር መረጃ የሰጡኝ ወይዘሮ አጸዶ ዳርጨ እና ወይዘሮ ፋልታም ኮሮሌ ስለእያንዳንዳቸው አሠራርና አዘገጃጀት የሚከተለውን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

**ባጭራ** (Bac'c'iraa):- ይህ ባህላዊ ምግብ በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት በተዓምር የማይቀር የምግብ ዓይነት ነው፡፡ ምክንያቱም በቶክ-ቤኣ በዓል ቀን ሰዎች ጠግበው ማደር የግድ ስለሆነና ይህ የምግብ ዓይነት ለዚህ አመቺ በመሆኑ ነው በማለት የመረጃ ምንጮቼ ይገልጻሉ፡፡ ባጭራ ከምንና እንዴት እንደሚሠራ የተጠየቁት የመረጃ ምንጮቼ ሲገልጹ ባጭራ በሁለት ዓይነት ዘዴ ሊሠራ ይችላል፡፡ አንድኛው ቆጮ በደንብ ተቆርጦ ከተዘጋጀ በኋላ በምጣድ ይነኮርና በሰል ሲል ቅቤና አይብ ቅመማ ቅመም ተጨምሮበት ቀዝቀዝ ሲል በህብረት የሚበላ ምግብ ሲሆን፣ ሁለተኛው የባጭራ ዓይነት ደግሞ አሠራሩ በመጀመሪያ ቆጮ ተቆርጦ ያልተነጠረ ቅቤ ተጨምሮበት የሚበላ ምግብ ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

**ኡታ** (Uttaa):- ኡታ ለቶክ-ቤኣ በዓል እንዴትና ከምን ይዘጋጃል ለሚል ጥያቄ ማብራሪያ እንዲሰጡ የተጠየቁት የመረጃ ምንጮቼ እንዲህ ይላሉ፡፡ በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት ከሚበሉ ምግቦች ዋነኛው አንዱ ኡታ (Uttaa) ሲሆን በዓይነቱ በሦስት የሚመደብ ሆኖ አንድኛው ኡታ (Uttaa) ከጤፍ፣ ከማሽላ ወይም ከበቆሎ ቂጣ ጋር አይብ፣ ቅቤና ቅመም ተጨምሮበት የሚሠራ የምግብ ዓይነት ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

ሁለተኛውን የኡታ (Uttaa) ዓይነት አሠራር ሲገልጹ ደግሞ ስሙ "ፋቲያ" (Faatiya) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ቀይ የጡንቻ ስጋ ተመርጦ በደንብ ተቀቅሎ ከበሰለ በኋላ ወጥቶ እንዲቀዘቅዝ ይደረጋል፡፡ አዘጋጇ ሴት እጇን በደንብ ታጥባ የበሰለውን የጡንቻ ስጋ ተልትላው ስትጨርስ በወጪት ውስጥ ከቅቤ፣ ከዓይብ እና ከቅመማ ቅመም ጋር አዋህዳ ለመብል ታቀርበዋለች፡፡ ሦስተኛው የኡታ (Uttaa) አሠራር ደረቅ ያለ የቀይ ስጋ ቋንጣ ይወቀጥና ከቅቤ፣ ከቅመማ ቅመም እንዲሁም ከአይብ ጋር ተዋህዶ በመሠራት በቶክ-ቤኣ በዓል ቀን በህብረት ይበላል በማለት ይገልጻሉ፡፡

**ሲሊሷ** (Siilissuwa):- በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት ከሚዘጋጁት ባህላዊ ምግቦች መካከል አንዱ ሲሊሷ (Siilissuwa) ሲሆን ስለሲሊሷ (Siilissuwa) አሠራር እንዲያብራሩ

የተጠየቁ የመረጃ አቃባዬ እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ "ሲሊሷ (Siilissuwa) በቶክ-ቤኣ በዓል ቀን ከሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦች የተለየ ክብር የሚሰጠውና የማይቀርም ሲሆን አሠራሩ አይብ ተጨምቆ አጓቱ ከወጣ በኂላ ደረቅ ሲል በወጪት በ(Shaata) ውስጥ ነጭ ሽንኩርትና ከሌሎች ቅመማ ቅመም ዓይነቶች ጋር የተነጠረ ቅቤ በዛ ተደርጎ ተጨምሮበት ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡ ይህንን ባህላዊ ምግብ ከማንኛውም ቂጣ ጋር መብላት የሚቻል ሲሆን ቅቤ ውሃ እስኪመስል ድረስ ተጨምሮ የሚሠራ በመሆኑ ከቂጣ ጋር ለአበላል ብዙም ስለማይመች በብሔረሰቡ በተለመደው ባህላዊ ማንኪያ (Mook'iya) እየተወሰደ የሚበላ ምግብ ነው፡፡ ማንኪያ በሌለበት አካባቢ ከተለበለበ ጎመን ጋር የሚቀርብ ሲሆን ይህም ተንጠባጥቦ ልብስን እንዳያበላሽ ታስቦ ነው፡፡" በማለት ያብራራሉ፡፡

**ታንጨዋ (Tanc'c'uwa)፡-** ታንጨዋ (Tanc'c'uwa) በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት ከሚዘጋጁት የምግብ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን ስለታንጨዋ (Tanc'c'uwa) አሠራር መረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁ መረጃ አቃባዮች እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡ "ታንጨዋ (Tanc'c'uwa) የጎመን ቅቅል ተከትፎ ከአይብ ከቅቤና ከቅመማ ቅመም ጋር ተዋህዶ ይዘጋጅና በቆጮ ተደርጎ በበዓሉ ወቅት በህብረት የሚበላ ምግብ ነው፡፡"

**ቡሊያ (Bulliya)፡-** በቶክ-ቤኣ በዓል ጊዜ ከሚቀርቡት ምግቦች ስለቡሊያ (Bulliya) አሠራር እንዲያብራሩ የተጠቁት መረጃ አቃባዬ ቡሊያ (Bulliya) ከጎመን ከቅቤ እና ከቅመማ ቅመም ተዘጋጅቶ በቆጮ ቂጣ ይባላል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

**ሼሊያ (Shelliya)**፡- በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት ከሚዘጋጁት ባህላዊ ምግቦች ስለሼሊያ (Shelliya) አሠራር ገለጻ እንዲያደርጉ የተጠየቁት የመረጃ ምንጩ እንዲህ ይላሉ፡፡ "ሼሊያ (Shelliya) በሁለት መንገድ የሚዘጋጅ ሲሆን አንድኛው ሀንጮቴ (Usuk'iya) ተቀቅሎ ከወጣ በኂላ ይለነቀጥና አይብ፣ ቅቤና ቅመማ ቅመም ተጨምሮበት በቂጣ የሚበላ ነው፡፡ ሁለተኛው የሼሊያ (Shelliya) ዓይነት ሀንጮቴ (Usuk'iya) ተቀቅሎ ይለነቀጥና ከባቄላ ወይንም ከአተር ቅቅል ጋር ተዋህዶ ቅቤና ቅመማ ቅመም ተጨምሮበት ከተዘጋጀ በኂላ በቆጮ ቂጣ ይበላል፡፡"

**የቆጮ ቂጣ (Unc'c'a ukitsaa)፡-** ለቶክ-ቤኣ በዓል የሚሆን ከእንስቶች መካከል ያበበ እንሰት ከሦስት ወር በፊት ተለይቶ እንዳይነካ በወገቡ በኮባ ታስሮ (ምልክት ተደርጎበት) ይቀመጣል፡፡ ይህ ተለይቶ የተቀመጠውን እንሰት ሶስት ወይም አራት

ሴቶች በጋራ በመሆን ለበዓሉ ሁለት ወር ሲቀረው ይፍቁታል፡፡ የፋቁትን ቆጮ ትልቅ ጉድጓድ ቆፍረው በኮባና በእንሰት ቅጠል አልብሰው እዚያው ውስጥ ይቀብሩትና ከአስራ አምስት ቀን ላላነሰ ጊዜ ይቆያል፡፡ በዓሉ ሲቀርብ ያንን የተቀበረውን ቆጮ በማውጣት በህብረት ይቆርጡታል፡፡ ያ የተቆረጠው ቆጮ በወፍራሙ ተደርጎ በትልቅ ምጣድ ተደፍቶ ከተለያዩ ማባያዎች ጋር በህብረት ይበላል፡፡ የቆጮ ቂጣ በቶክ-ቤኣ በዓል ቀን በዋናነት ከሲሊሷ፣ ከታንጩዋ፣ ከቡሊያ፣ ወዘተ ማባያዎች ጋር ይበላል በማለት ስለአሠራሩ መረጃ የሰጡኝ ወይዘሮ አጸዶ ዳርጩ ይገልጻሉ፡፡

**የጤፍ ቂጣ** (Gashe ukitsaa)፡- የጤፍ ቂጣ በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት ከተለያዩ ማባያዎች ጋር ከሚቀርቡ ባህላዊ ምግቦች አንዱ ሲሆን ስለአዘገጃጀቱና አሠራሩ መረጃ የሰጡኝ ወይዘሮ ፋልታም ኮፎሌ አሁን ዘመኑ ተሻሽሎ በዘመናዊ ወፍጮ ይፈጫል እንጂ ዘመናዊ ወፍጮ በሌለበት ዘመን በዓሉ ሲደርስ ጤፍ ተወቅጦ በአካባቢው ላሉ ወጣት ሴቶች በቂል ተደርጎ ይከፋፈልና ተባብረው ፈጭተው ይመልሳሉ፡፡ ምክንያቱም ለበዓል ብዙ ጤፍ ስለሚያስፈልግ ያንን ሁሉ በጥቂት ሰዎች ጉልበት ብቻ መፍጨት ከባድ ስለሚሆን በዚህ መልኩ የተፈጨው ጤፍ ተሰብስቦ ቂጣ ተሰርቶ በዋናነት ከኡታ ጋር በህብረት ይበላል በማለት ይገልጻሉ፡፡

**የእሸት በቆሎ ቂጣ** (Salkketsaa)፡- በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት ከሚቀርቡ ባህላዊ ምግቦች ውስጥ አንዱ ስለሆነው ስለእሸት በቆሎ ቂጣ (Salkketsaa) መረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁ ወይዘሮ አጸዶ ዳርጩ "Salkketsaa" በዓሉ የሚከበርበት ወቅት የበቆሎ እሸት የሚደርስበት ወቅት በመሆኑ ጠንከር ያለ በቆሎ ተመርጦ ይቆረጥና ማጭድ ወይም ትልቁ ቢላዋ በበጥንቃቄ ታጥቦ ከጸዳ በኂላ የእንሰት ቅጠል ተዘርግቶ በዚያው ላይ በማጭድ ወይም በበትልቁ ቢላዋ እየተቆረጠ ይፈለፈላል፡፡ ተፈልፍሎ ካለቀ በኂላ ትንሽ ውሃ ተነስንሶበት ለአስራ አምስት ደቂቃ ያህል በቅጠል ተጠቅልሎ ይቀመጥና ከአስራ አምስት ደቂቃ በኂላ በንጹህ ድንጋይ ወፍጮ ይዳጣል፡፡ ልክ በረድ የሚመስለው ተድጦ ያለቀው በእንሰት ቅጠል ተሸፍኖ በሸክላ ምጣድ ይጣድና ሲበስል ከማባያዎች ጋር ይበላል ይላሉ፡፡

**ቦሩዋ** (Booruwa)፡- በቶክ-ቤኣ በዓል አከባበር ወቅት ከማይቀሩ ባህላዊ ምግቦች አንዱ ቦሩዋ (Booruwa) ሲሆን ስለቦሩዋ (Booruwa) አሠራር እንዲያብራሩ በድጋሚ የተጠየቁት ወይዘሮ አጸዶ ዳርጩ እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ ቦሩዋ

(Booruwa) ከበቆሎ፣ ከጤፍ፣ ከአጃ… ሲዘጋጅ ይችላል። አዘገጃጀቱ እነዚህ እህሎች በደንብ ደቅቀው ከተፈጩ በኋላ ተቦክቶ ለትንሽ ጊዜ ኩፍ ካለ በኋላ ለጋ የእንሰት ቅጠል ተቆርጦ ይሰበሰብና በዚያ ቅጠል ተጠቅልሎ በትልቅ እንስራ ተደርጎ ይቀቀልና የተቀቀለውን ቅጠሉን ቀስ ተደርጎ ይወገድና ሰፋ ባለ መሶብ ቀርቦ ከተለያዩ ማባያዎች ጋር በህብረት የሚበላ ባህላዊ የበዓል ምግብ ነው በማለት ይገልጻሉ።

**የጎደሬ ቅጥቅጥ (ጫዲያ) (C'ad'd'iya)**፡- *ጫዲያ* (C'ad'd'iya) በቶክ-ቤኣ እለት ከሚቀርቡ ከተለመዱ ምግቦች አንዱ ሲሆን ስለአሠራሩ የተጠየቁት የመረጃ ምንጮቼ ሲገልጹ "*ጫዲያ* (C'ad'd'iya) ከጎደሬና እና ከእንሰት ስር (አምቾ) የሚሠራ እንደሆነና አሠራሩም ከጎደሬ የሚሠራው *ጫዲያ* (C'ad'd'iya) ጎደሬ ተቀቅሎ ይዳጥና ከሲሊሶ ጋር የሚበላ ሲሆን ከአምቾ የሚሠራ *ጫዲያ* (C'ad'd'iya) ደግሞ አምቾ ተቀቅሎ ልክ እንደ ጎደሬ ተድጦ ከበርበሬ ዳጣ ጋር በህብረት ይበላል።" ይላሉ።

በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት ተዘጋጅተው ስለሚቀርቡ ባህላዊ መጠጦች መረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁት ወይዘሮ አጸዴ ዳርጩ እና ወይዘሮ ፋልታም ኮፎሌ እንዲህ ሲሉ መረጃ ይሰጣሉ።

ከመጠጡ በብዛት የተለመደና ለቶክ-ቤኣ በዓል የሚዘጋጅ መጠጥ "ቦርዴ"፣ እና "Sid'id'uwa" (ከጤፍ ብቻ የሚዘጋጅ መጠጥ) ሲሆን ከምኒሊክ ወረራ (1883) ወዲህ ደግሞ የጌሾ ጠላ እየተለመደ መጥቷል። ግን አሁንም ቢሆን በተለይ "Sid'id'uwa" (ከጤፍ ብቻ የሚዘጋጅ መጠጥ) ተዘውትሮ ይዘጋጃል ይላሉ።



ምስል ሦስት፡- ለቶክ-ቤኣ በዓል የሚዘጋጁ በየአይነት የምግብ ዘሮች፤

እነዚህ አብዛኞች የምግብ ዓይነቶች ከፍ ሲል አዘገጃጀታቸው የተብራራ ሲሆን በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት የማይቀሩ ናቸው ሲሉ የመረጃ ምንጮች ይገልጻሉ፡፡



ምስል አራት፡- ከእንስሳት ተዋጽኦዎች፣ ከስራስር እና ከቅጠላቅጠሎች ለቶክ-ቤኣ በዓል የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦች፤

እነዚህ በዳውሮ ብሔረሰብ ዘንድ ለቶክ-ቤኣ የሚዘጋጁ ምግቦች ሲሆኑ አዘገጃጀታቸው ከፍ ሲል ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ ባህላዊ ምግቦቹ ከእንስሳት ተዋጽኦዎች፣ ከስራስርና

ከቅጠላቅጠል የሚዘጋጁ ሲልሲ፣ ቡራቷ፣ ኡታ፣ ታንጨዋ፣ ቡሊያ፣ የጎደሬ ቅጥቅጥ (C'ad'd'iya) እና ሼሊያ እንደሆኑ ከሰነድ ፍተሻው የተገኘ መረጃ ያሳያል፡፡



ምስል አምስት፡- ቦሩዋ (Booruuwa) ከእጃ የተዘጋጀ በቶክ-ቤኣ በዓል ቀን የሚቀርብ ባህላዊ ምግብ፤

ቦሩዋ (Booruuwa) ሌላው በቶክ-ቤኣ በዓል ጊዜ የማይቀር ባህላዊ ምግብ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች የሚያብራሩት ሲሆን ቦሩዋ (Booruuwa) የሚዘጋጀው በእጃ ብቻ ሳይሆን ከበቆሉና ከጤፍም ሊዘጋጅ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡

#### 4.1.6. የቶክ-ቤኣ በዓል ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ

በዳውሮ ብሔረሰብ ዘንድ ቶክ-ቤኣ ለምን ዓላማ እንደሚከበርና ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳው ምን እንደሆነ እንዲያብራሩ የተጠየቁ ኢራሻ ደስታ ጦሩ የሚከተለውን ያብራራሉ፡፡

የቶክቤኣ በዓል የሚከበርበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ዓመቱ እኛን ስለጠበቀ እኛም ዓመቱን በክብር ሸኝተን አዲሱን ዓመት በደስታ መቀበል አለብን የሚል አንድምታ አለው፡፡

በአሮጌ ዓመት ማብቂያ ዕለት በልቶ ጠግቦ ያልተኛ ሰው ተመዝኖ ከቀለለ የአሮጌ ዓመት የነበረ መጥፎ ነገር ወደ አዲሱ ዓመት ይሸጋገራል ተብሎ ስለሚታመን የቶክቤኦ በዓል ጠግቦ በመብላት በደስታ እና በጥጋብ ይከበራል፡፡

በዋናነት ግን ምክንያቱ በአዱሱ ዓመት ጠግቦ ለመክረም፣ ቤተሰብ፣ ጎረቤት፣ አገር… ወዘተ ሰላም እንዲሆን የሚለውን ምኞት ለመግለጽ ነው፡፡ ሀብት፣ ልጆች በሰላም ስለከረሙ አምላክን ለማመስገን አዱሱ ዓመት የደስታ፣ የሠላምና የበረከት ዘመን እንዲሆን በመመኘት ቶክ-ቤኣ ይከበራል፡፡

እንደ መረጃ ምንጮች ገለጻ በዳውሮ ብሔረሰብ ባህል ቂም የያዘ ወይም ከሰዎች ጋር የተጣላው ሰው ከተጣላው ሰው ጋር እርቅ ሳያሰደርግ አዲሱን ዓመት የሚቀበል ከሆነ ዓመቱ እንጂ ሰውዬው አልታደሰም የሚል አንድምታ አለው፡፡ በሌላ መልኩ ቆሻሻን ይዞ አዲስ ልብስ እንደ መልበስ ይቆጠራል ይላሉ፡፡ ስለሆነም አዲስ ዓመት ሳይመጣ በተጣሉ ሰዎች መካከል የእርቅ ስርዓት ይደረጋል፡፡ ምንም እንኳ ይህ ስርዓት ባህላዊ ቢሆንም ከአባቶች ጀምሮ የተጣሉ ሰዎችን ለማስታረቅ አንዱ መንገድ ሲሆን ቆይቷል ይላሉ፡፡

በተጨማሪ ቶክ-ቤኣ ሲደርስ ከባሏ የተፋታች ሴት በብትኖር እንኳ የደረሰ ልጅ ካለ በልጁ አማካይነት፣ ሚዜያቸው (Miyaata) ካለ በሚዜያቸው አማካይነት፣ ካልሆነም በሽማግሌ አማካይነት ታርቀው አንድ በመሆን በዓሉን በጋራ ያከብራሉ ሲሉ ኢራሻ ደስታ ጦፉ ተጨማሪ ቶክ-ቤኣ ለማስታረቅ ያለውን ሚና ያብራራሉ፡፡

ኢራሻ ድስታ ሲሉ በሌላ መልኩ ቶክ-ቤኣ በጋራ የሚያከብሩት በዓል እንደመሆኑ መጠን ብዙ ማህበራዊ ተራክቦዎች ይኖራሉ፡፡ ለቶክ-ቤኣ በዓል እርድ የማይቀር ሲሆን ለእርድ የሚሆን ገንዘብ ዓመቱን ሙሉ በአንድ አካባቢ ያሉ አባወራዎች መሪ በመሰየም በጋራ ገንዘብ የማሰባሰብ ሥራ ይሰራሉ፡፡ በዚህ ሂደት ስለኑሯቸው፣ ስለአካባቢያቸው፣ ስለእድገታቸው ይመካከራሉ፡፡ በዓሉ በሚከበርበት ዕለት ወጣት ወንዶችና ሴቶች ቤት ለቤት እየዞሩ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ ሽማግሌዎች በጥላ ስር (Dubbusha) ውስጥ በመሆን በአዲሱ ዓመት ሊያከናወኑ ስላሰቡ ጉዳዮች በጋራ ሲመክሩ ይውላሉ፡፡ በቆይታቸውም ስለሀገራቸው፣ ስለመንግስታቸው፣ ስለአካባቢያቸው፣ ስለሚዘንበው ዝናብ፣ ስለሚነግዱ ነጋዴዎች፣ ስለአራሽ ገበሬ፣ ስለሚማረው ተማሪ፣ ስለሚዘራው አዝርእትና ስለእርሻው እየጸለዩ፣ ያለፈው ዓመት ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆንም ያሻገራቸውን አምላካቸውን እያወደሱ ያከብሩታል፡፡

በዓሉ ለማህበረሰቡ ምን ዓይነት ማህበራዊ ፋይዳ እንዳለው ማብራሪያ የሰጡት እነዚህ መረጃ ሰጪዎች ሲገልጹ በዓሉ ዓመቱን በሙሉ በሥራ የደከመ አፅምራቸውን በሙሉ ተስፋ ሠንቀው እንዲነሱ ያደርጋል፤ ህብረተሠቡ የበዓል መከበር በአካባቢው ትልቅ በረከትና መነሳሳትን ይፈጥራል ብሎ ያምናል። የበዓሉ አለመከበር ለግለሰቡም ሆነ ለአከባቢው ችጋር ያበዛል ተብሎ ይታመናል በማለት ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ የቶክ-ቤኣ በዓል ወይም ‹ላይታ ላሚያ› የተራራቁት የሚገናኙበት፣ የተጣሉ የሚታረቁበት፣ ያዘኑ የሚደሰቱበት፣ ተስፋ የቆረጡ ተስፋቸውን የሚሰንቁበት፣ የተራቡ ጠግበው የሚበሉበት እና የሰዎች ማህበራዊና መንፈሳዊ አንድነታቸው በይበልጥ ተጠናክሮ በአዱሱ ዓመት በአዲስ መንፈስ ለሥራ እንዲነሱ የሚደረግበት፣ አገርን፣ ቤተሰብን፣ ልጆችን፣ ንብረትን… ወዘተ ጠብቆ ከዓመት ያሻገረውን አምላክ በማመስገን እየበሉና እየጠጡ ለመደሰትና አዱሱ ዓመት በታደሰ መንፈስ ለመቀበል የሚያከብሩት በዓል ነው ሲሉም የበዓሉን ማህበራዊ ፋይዳ ያብራራሉ።



ምስል ስድስት፡- አባወራዎች በጋራ ሆነው ቶክ-ቤኣን በጥላ ስር (Dubbushaa) ላይ ሆነው የሚያከብሩበትን የሚያሳይ ፎቶ ተፈጥሯዊ ባልሆነ መቼት የተዘጋጀ፤

(ፎቶ በአፈወርቅ ማኖሶ)

በምስሉ ላይ እንደተመለከተው ወንዶችን እያስተናገዱ ካሉ ሴቶች ውጪ አብሯቸው ያሉት ሌሎች ሴቶች የሉም፡፡ ይህ የሆነበትን ምክንያት የተጠየቁት መረጃ ሰጪዎች እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

አባወራዎች በዓሉን ምክንያት በማድረግ እየበሉና እየጠጡ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳያቸውን፣ የአዲስ ዓመት ዕቅዳቸውን፣ ባሳለፉት ዓመት የገጠማቸውን ችግሮችን እንዴት እንዳለፉትና ከእንደዚያ አይነት ችግሮች እንዴት ማለፍ እንዳለባቸው እየመከሩ፣ የቀጣይ በዓላቸው እርድ ማን በራፍ መሆን እንዳለበት እየወሰኑ፣ እንዲሁም የተጣሉ ካሉ እያስታረቁ በጥላ ስር (Dubbushaa) ላይ ለብቻቸው ያከብራሉ፡፡ ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ከሴቶችና ከወጣቶች ይልቅ አባወራዎችን የሚመለከቱ ናቸው በማለት ያብራራሉ፡፡



ምስል ሰባት፡- ሴቶች (እናቶች) በጋራ ሆነው ቶክ-ቤኣን የሚያከብሩበትን የሚያሳይ ፎቶ ተፈጥሯዊ ባልሆነ መቼት የተዘጋጀ፤ (ፎቶ በአፈወርቅ ማኖሶ)

ምስል ሦስት ላይ እንደተመለከተው ሴቶች ቶክ-ቤኣን በጋራ ሆነው ሲያከብሩ ያሳያል፡፡ ይህንን በተመለከተም መረጃ ሰጪዎች ሲያብራሩ ሴቶችም ቶክ-ቤኣን ሲያከብሩ ልክ እንደ ወንድ አባወራዎች የሚመክሩበት የራሳቸው የሆነ ጉዳይ አላቸው፡፡ ስለሆነም ለብቻቸው በመሆን ለበዓል የተዘጋጀውን ምግብ እየበሉና

እየጠጡ ቀጣይ የቅቤ መግዣ ገንዘብ ከመቼ ጀምሮ መሰብሰብ እንዳለባቸውና ሌሎችም ጉዳዮችን ይመክራሉ፤ ምክንያቱም በዳውሮ ብሔረሰብ ባህል አባወራ ለእርድ ገንዘብ ሲሰበስብ ሴቶች ደግሞ ለበዓል የሚሆን ቅቤ መግዣ የማዘጋጀት ሀላፊነት አለባቸው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

### 4.1.7. በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት የሚከወኑ ትዕምርታዊ ክዋኔዎች ትርጉም

ከመረጃ ምንጮቼ መካከል ዘርሁን (የዞኑ ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያና) እና ኢራሻ ደስታ በተመሳሳይ ከቶክ-ቤኣ በዓል አከባበር ጋር ተያይዞ ስለሚከናወኑ ትዕምርታዊና ባህላዊ ክዋኔዎች ትርጉም ሲገልጹ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

በበዓሉ እለት ዋዜማ ማታ ቤተሰብ ተሰብስበው ከየዓይነቱ የተዘጋጁ ምግቦችንና መጠጦችን ከመብላትና ከመጠጣቱ በፊት አንድ ስርኣት ይከናወናል፡፡ የቤቱ አባወራ ወይም የሞተ ከሆነ  የቤተሰቡ ታላቅ ወንድ ልጅ አንድ ችቦ እሳት ይዞ የቤቱን ምሰሶ፣ የከበብት ግድግዳና የቤቱን በርና መስኮት  እየነካካ ክፉ መንፈስ ይውጣ፣ የአሮጌ ዓመት ችግር፣ ማጣት፣ በሽታ፣ ጥላቻ፣… ከቤቴ፣ ከልጆቼ፣ ከእንስሳት፣… ውጣ! እያለ፣ አዲሱ ዓመት ለቤተሰቡ፣ ለእርሻዉ፣ ለከብቶቻቸው፣ ለጎረቤቱና ለሀገሩ ሁሉ የሰላም፣ የጤናና የጥጋብ እንዲሆን በመመኘት ከመረቀ በኋላ የአሮጌው አመት ከነችግሩ ማለፉን ለማመልከት በእጁ የያዘውን እሳት ውጪ አውጥቶ ይወረወራል፡፡ ይህም ክዋኔ አሮጌ ዓመት ማብቃቱንና አዲስ ዓመት መግባቱን የማብሰሪያ ምልክት ነው፡፡ ከዚያም ቤተሰቡ እየተዝናና እየተጫወተ በልቶ ጠግቦ ያድራል፡፡

በቶክ- ቤኣ በዓል ወቅት ከሚከወኑ ክዋኔዎች ዋናኛው በታላላቅ ሰዎች የሚደረግ የምስጋና እና የምርቃት ስነ-ስርዓት ሲሆን የምስጋና ስነ-ስርዓቱ ትርጉም ጨለማ የነበረውን ክረምት በሞት፣ በበሽታ ሳይቀጥፋቸው አበባ የፈካበትን፣ ወንዝ የጎደለበትን ብሩህ ወቅት ላሳያቸው አምላክ ምስጋና ማቅረብ ሲሆን የምርቃት ስነ-ስርዓት ትርጉሙ የሚመጣው አዲሱ ዓመት በዓለም፣ በሀገር፣ በአካባቢው፣ በመንደር ሞት፣ በሽታ፣ ስደት፣ ረሃብ፣ ችግር እንዳይከሰትና ሰዎችም ሆነ እንስሳት ዓመቱን በሠላም እንዲከርሙት የሚደረግ የተማጽኖ ሥርዓት ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት ከሚከወኑ ክዋኔዎች ሌላው ዳጋ (Dagaa) በአንድ መጠጫ ለሁለት ሆነው መጠጣት ሲሆን ይህም ሰፋ ያለ ቂል ተዘጋጅቶ ለሁለት

በተሰነጠቀው ቅል (Shambbaa) ቦርዴ ወይም ከጤፍ የተዘጋጀው መጠጥ (Sid'id'uwa) ተጨምሮ ሁለት እኩያ የሆኑ ሰዎች ለሁለት በአንድ በተሰነጠቀው ቂል (Shambbaa) በጋራ የሚጠጡበት ሲሆን የዚህ ክዋኔ ትርጉሙ ፍቅርንና አንድነትን የሚያመላክት እንደሆነ አቶ ዘርሁንና ወይዘሪት ስንቅነሽ (የዞኑ ባህል ቱሪዝም ባለሙያዎች) በተጨማሪ ይገልጻሉ።

በተጨማሪም በቶክ-ቤኣ በዓል አከባበር ወቅት ለበዓሉ ማድመቂያ የሚሆኑ የተለያዩ ክዋኔዎች የሚደረጉ ሲሆን፤ ስለእነዚህ ማድመቂያዎች መረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁ ኢራሻ ደስታ ጦፉ እና አቶ ዶግሶ ዶልኣሞ እንደሚከተለው ያብራራሉ።

ለበዓሉ የተዘጋጁ ምግቦችንና መጠጦችን ከተመገቡ በኋላ መንደች ልጆች የተለያዩ ዜማዎችን እያዜሙና እየጨፈሩ ከዘመድ ቤት ወደ ዘመድ ቤት፣ ከሰፈር ወደ ሰፈር፣ ከጎረቤት ወደ ጎረቤት በመዟዟር ስጦታ እየሰበሰቡ የእንኳን አደረሳችሁ ደስታቸውን በዜማቸው እያቀነቀኑ፣ ባህላዊ ጭፈራዎችን እያሳዩ ደስታቸውን ይገልጻሉ። እነዚህ ልጆች በየገቡበት ሁሉ የተለያዩ ባህላዊ የምግብ ዓይነቶችን እንዲመገቡ ይጋበዛሉ። ሰፈር ለሰፈር ሲዞሩ ከሚያዜሙት ባህላዊ ዜማዎች መካከል፡-

> Silo silo baalay baana ge ho…. ho…ho… silo (ስሎ ስሎ ባላይ ባና ጌ ሆ…ሆ… ሆ… ስሎ)፣
> Silo silo laytsi yaana ge ho…. ho…ho… silo (ስሎ ስሎ ላይት ያና ጌ ሆ…ሆ… ሆ… ስሎ፣)
> Silo silo baalay barata ho…. ho…ho… silo (ስሎ ስሎ ባላይ ባራታ ሆ…ሆ… ሆ… ስሎ)፣
> Silo silo laytsi hannooda ho…. ho…ho… silo (ስሎ ስሎ ላይት ሃኖዳ ሆ…ሆ… ሆ… ስሎ)፣

እነዚህ ባህላዊ ግጥሞች በአማርኛ ሲተረጎሙ፡-

በዓል እሄዳለሁ ይላል፣

የዛሬ ዓመት እመጣለሁ ይላል፣

በዓል ውድ ነው፣

የዛሬ ዓመት የዚህን ጊዜ ነው፣ እያሉ እያዜሙ እንደሚዞሩ ይገልጻሉ፡፡

በዋዜማው ምሽት እንሶስላ (Wosolluwa) ጣቶቻቸውን ተቀባብተው የተዋቡ ልጃገረዶችም የሌሊት ወጋገን ሲፈካና ሲነጋ አንድ ላይ በመሰብሰብ የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን እየዘፈኑ እንደ ወንዶች ልጆች ከሰፈር ሰፈር እየተዟዟሩ መልካም ምኞታቸውንና የእንኳን አደረሳችሁ ደስታቸውን ይገልጻሉ፡፡

የልጃገረዶቹ እንኳን አደረሳችሁ መልካም ምኞት ጨዋታ ከአንዱ ቤት ወደ አንድ ቤት እየተኬደ እንደመሆኑ መጠን እንደ ወንዶች ልጆች የገንዘብ ስጦታን አይቀበሉም፡፡ ሆኖም የምግብና የመጠጥ ግብዣ ይቀበላሉ፡፡ በዕለቱም ጠግበው ይውላሉ፡፡ በጨዋታቸው ጊዜ ወንዶችና ሴቶች በየቡድናቸው ሆነው የተለያዩ ባህላዊ ዜማዎችን ይጫወታሉ፡፡

ልጃገረዶች ከሚያዜሙ ባህላዊ ዜማዎች መካከል የሚጠቀሱት፡-

Hayyayya hayyaa gadile (2x) (*ሀያያ ሃያ ጋዲሌ* (2x)፣

Gadiliyaw gaac’c’o gaashatto gadaraw komppa betsekkee (*ጋዲሊያው ጋጬ ጋሻቶ ጋዳራው ኮምፓ በቴኬ*)፣

እያሉ የሚያዜሙ ሲሆን፤ትርጓሜው "*ጋዲሊያ*" ማለት በዓል ማለት ሲሆን "*ጋዲሊያው ጋጬ ጋሻቶ ጋዳራው ኮምፓ በቴኬ*" ማለት ለበዓል የተፈጨውን ጤፍ ለወጣቱ ወይም ለምትወደው ልጅ ጋግራ ጨረሰች የሚልን ፍች ይሰጣል ሲሉም ይገልጻሉ፡፡

## 4.2. የዳውሮ ማህበረሰብ ለቶክ-ቤኣ በዓል ያለው አመለካከት

ቶክ-ቤኣ የዳውሮዎች ጥንታዊ ስልጣኔ በዘመን አቆጣጠር ቀመር ከምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ማሳያ እንደሆነ ዩኒክ ኢትዮጵያና ሌሎች ከሰነድ የተገኙ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ይህ ጥንታዊ ስልጣኔ በማህበረሰቡ ዘንድ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ እስካሁን የመጣ ሲሆን ስልጣኔውን በተመለከተ ማህበረሰቡ ስላለው አመለካከትና በዓሉ ባህላዊ ቅርጹን ይዞ ለትውልድ እንዲተላለፍ ምን አይነት አስተያየት እንደሚሰጡ እንዲያብራሩ የተጠየቁት መረጃ ምንጩ ኢራሻ ደስታ ጦፉ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

"በዓሉ ጥንት አባቶቻችን ፈጣሪ በሰጣቸው ጥበብ ቀናትን ቆጥረው፣ ጨረቃ የምትወጣበትንና የምትገባበትን ቀናት ስሌት ሰርተው አዲስ ዓመት የሚያከብሩበት ነው፡፡ በዓሉን ሲያከብሩም እንደ አሁኑ ዘመን የተለያዩ ሃይማኖቶች ባልተስፋፉበት አሮጌውን ዓመት ያሳለፋቸውን አምላካቸውን የሚያመሰግኑበት፣ አዲሱን ዓመት እንዲባርክላቸው ደግሞ የሚለምኑበት ነው፡፡ በእርግጥ በዘመኑ እንደ አሁኑ ለይተው በተለያዩ ስም የሚጠሩት አምላክ የላቸውም፤ የሚጠሩት፣ የሚያመሰግኑትና የሚለምኑት ፈጣሪ በሚል ስም ብቻ ነው፡፡ አሁን ደግሞ የተለያዩ ሃይማኖቶች ፈጣሪያቸውን እንደየአምልኮታቸው በተለያየ ስም ይጠሩታል፡፡ ስለሆነም በተለይ የአሁኑ ትውልድ በዓሉን ከባዕድ አምልኮ ጋር ያያይዛል፡፡ ቢሆንም መታወቅ የሚገባው በዓሉ ባህላዊ እንጂ ከባዕድ አምልኮ ጋር የሚያስተሳስር ምንም ነገር የለውም" በማለት ይገልጻሉ፡፡

ስለዚህ ጉዳይ ማብራሪያ እንዲሰጡ የተጠየቁት አቶ ታዬ እና ወይዘሮ አዲሴ (የዞን ባህል ቱሪዝም ባለሙያዎች) በተመሳሳይ "ቶክ-ቤኣ እኛ ስንወለድ አባቶች እያከበሩና ለልጆቻቸው ሲያስተላልፉ የነበሩት በዓል እንደመሆኑ መጠን በበዓሉ አከባበር ወቅት ከባዕድ አምልኮ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለውም፤ አንዳንድ ግለሰቦች ከቶክ-ቤኣ ትርጓሜው ጋር ተያይዞ ተሸክሞ ማየት የሚለውን እያነሱ ተሸክሞ የሚያየው እርኩስ መንፈስ ነው የሚል አንድምታ በራሳቸው የሚሰጡ ቢሆንም እነሱ እንደሚሉት ተሸክሞ የሚያየው መንፈስ ሳይሆን ጠግቦ በልቶ ያላደረውን የመጣው አዲሱ ዓመት እስኪያልቅ ያቀለዋል ወይም ጥጋብ የለውም የሚል አንድምታ እንጂ ሌላ ምንም መንፈስ ወይም አምልኮ የለውም" ሲሉ ያብራራሉ፡፡

በተጨማሪም በዓሉ ባህላዊ ቅርጹን ይዞ ለትውልድ እንዲተላለፍ ምን አይነት ሀሳብ እንደሚሰጡ የተጠየቁት ኢራሻ ደስታ ጦፋ "በእርግጥ አሁንም ቢሆን የበዓሉ አከባበር ሂደት ድሮ ዘመን የነበሩ በርካታ ነገሮች እያጣ መጥቷል፡፡ ለምሳሌ፡- እንደ ድሮ ዘመን ወንዶችና ሴቶች ወጣቶች ቤት ለቤት እየዞሩ፣ የበዓል ዘፈን እየዘፈኑ፣ የሚቀርብላቸውን ምግብ እየበሉ፣ ገንዘብ የሚሰበስቡበት ባህል እየቀረ መጥቷል፡፡ አሁን አሁን እንደ ድሮ ሴት ልጃገረዶች እንሶስላ (Wosolluwa) ጣቶቻቸውን ተቀብተው በቅጠል ጠቅልለው አድረው ሲነጋ ያንን ቅጠል ፈተው ጥለው ሰፈር የሚዞሩበትም ባህል የለም፡፡ አሁን ልጃገረዶች ጣቶቻቸውን የሚያስውቡት በተለያዩ ቴክኖሎጂ ባመጣቸው ቀለማት ነው፡፡ አሁን የቀረን አባወራዎች በጋራ የሚያደርጉት

የእርድ ስነ ስርዓት ብቻ ነው እንጂ ለበዓሉ ይዘጋጁ የነበሩ ባህላዊ ምግቦችም እንደ ድሮ በሙሉ እየተዘጋጁ አይደሉም፡፡ ስለሆነም ይህ እንቁ ባህል እንዳይበከልና ባህላዊ ቅርጹን ይዞ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ በተለይ ከተለያዩ ሰነድና መዛግብት እየተፈተሹ በሚመለከታቸው አካላት በኩል ለማህበረሰቡ ተገቢ ግንዛቤ ቢሰጥ የተሻለ ይሆናል፡፡" በማለት አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡

በዓሉ ባህላዊ ቅርጹንና እሴቱን ይዞ እንዲቀጥል ምን ዓይነት አስተያየት እንደሚሰጡ የተጠየቁት አቶ መብራቱ (የዞን ባህል ቱሪዝም ባለሙያ) በተጨማሪ ሲገልጹ በዓሉ አባቶች ከጥንት ጀምረው ሲያከብሩና ለልጆቻቸው ሲያስተላልፉ የመጡት በመሆኑ የነበረውን ባህላዊ ቅርጹን ይዞ እንዲቀጥል በርካታ ጥናቶች ሊጠኑ ይገባል፡፡ በተለይ ከጥናትም በተጨማሪ ሚዲያ የህዝብን እይታ ለማስፋት ትልቅ ሀይል ስላለው ከማህበራዊ ሚዲያዎች በተጨማሪ ትላልቅ መገናኛ ብዙሃን ሚዲያዎች ላይ የማስተዋወቅ ስራ በሰፊው ሊሠራ ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡

በመጨረሻም አሁን እንደ መንግስት ቶክ-ቤኣን በዓለም ባህል፣ ቅርስና ታሪክ መዝገብ (UNSCO) ለማስመዝገብ የተጀመረው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ቢቀጥልና ከውጤት ላይም ቢደርስ ይህን እንቁ ባህል ከአካባቢው አልፎ ለሀገር የሚኖረውን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ ያሰፋል በማለት መረጃ ሰጪዎች ተጨማሪ አስተያየታቸውን አክለዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያ፣ ግኝትና አስተያየት

ይህ ምዕራፍ ባለፉት አራት ምዕራፎች የተከናወኑ ተግባራት ማጠቃለያ የሚያገኙበት፣ የጥናቱ ግኝት የሚቀርብበት እና ግኝቱን መሠረት ያደረጉ አስተያየቶች የሚቀርቡበት ክፍል በመሆኑ ማጠቃለያ፣ የጥናቱ ግኝትና አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 5.1. የጥናቱ ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዳውሮ ብሔረሰብ ዘንድ የሚከበረውን የዘመን መለወጫ ቶክ-ቤኣ በዓል ክወና ሥርዓትን መተንተን ነበር፡፡ በንዑስነት ደግሞ የቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል ለብሔረሰቡ ያለውን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ መተንተን፤ በበዓሉ ወቅት የሚደረጉ ክዋኔዎች ትርጉም መግለጽ፤ በዓሉ በማህበረሱ ዘንድ ያለውን ትዕምርታዊ ትርጉም ማብራራት የሚሉት ዓላማዎች ቀርበው ነበር፡፡ ይህንን አብይ ዓላማና ንዑሳን ዓላማዎችን ለማሳካት በመስክ ምልከታ፣ በመዛግብት ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ጥናቱ ተንታኝ ገላጭ የጥናት ንድፍ የተከተለ ሲሆን በአይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ ለጥናቱ ታማኝ መረጃ እንዲሰጡ በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ አስር መረጃ ሰጪዎች ተመርጠው መረጃው ከላይ በተጠቀሱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስቧል፡፡

በመስክ ምልከታ፣ በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች የበዓሉን (የቶክ-ቤኣን) ትርጉም፣ ቶክ-ቤኣ የሚከበርበትን ቀን፣ ቶክ-ቤኣ ለማህበረሰቡ ያለውን ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ፣ ለቶክ- ቤኣ የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት፣ በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት የሚከወኑ ትዕምርታዊ ክዋኔዎች ትርጉም፣ ለቶክ-ቤኣ በዓል የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች የሚመለከቱ ሲሆን ከመስክ ምልከታ ከተገኘው ግንዛቤ፣ ከመረጃ ሰጪዎች ማብራሪያና ገለጻ፣ ከሰነድ ፍተሻ በተገኙ ሀሳቦች መረጃው ተብራርቶና ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በመጨረሻም የዳውሮ ማህበረሰብ ለቶክ-ቤኣ በዓል ያለው አመለካከት ከመረጃ ሰጪዎች አስተያየት መነሻ ተብራርቶ፣ ቢደረግ የተሻለ ነው የሚሉ አስተያየቶችም ታክለውበታል፡፡

## 5.2. የጥናቱ ግኝት

በምዕራፍ አራት የተብራራውን የመረጃ ትንተና መሠረት ያደረጉ የጥናት ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ከትርጉም አንጻር "ቶክ-ቤኣ" ማለት ጥሬ ትርጉም ተሸክሞ ማየት ወይም መዝኖ ማየት ማለት እንደሆነና ለዚህም ሲባል ሰውና እንስሳትን ጨምሮ ጠግበው በልተው እንደሚያድሩና ቤት ውስጥ ያሉ ሁሉም የቤት ዕቃዎች በምግብና በመጠጥ ተሞልተው የሚያድሩ መሆናቸውን መረጃው አሳይቷል፡፡

ቶክ-ቤኣ ወይም የዳውሮ ብሔረሰብ ዘመን መለወጫ (Laytsa laamiya) በዳውሮ አቆጣጠር (Dawuro payduwa wogaa) የጨረቃ መውጣትና መግባትን መሠረት ያደረገ የቀን አቆጣጠር ሲሆን የጨረቃ ይዘት፣ ቅርጽና መልክ እንዲሁም የመውጫ ሰዓት መቀያየርን ተከትሎ ጊዜን የመቁጠርና የመተንበይ ጥበብን የሚያካትት መሆኑን ከመረጃ ምንጮች የተገኘ ውጤት አመላክቷል፡፡

ቶክ-ቤኣ ወይም የዳውሮ ብሔረሰብ ዘመን መለወጫ ልክ እንደ አብዛኞቹ ሀገራት ዘመን መለወጫ በዓል አስራ ሁለት ወራትን (365/366 ቀናትን) አልፎ የሚመጣ በዓል መሆኑን መረጃው አሳይቷል፡፡

ቶክ-ቤኣን ለማክበር ቀናትንና ዓመትን ሲያልፉ አንድን ቀን (Guurraa) ንጋት፣ (Wonttaa) ጥዋት፣ (Gallassaa) ረፋድ፣ (Awa kawutuwa) ቀትር፣ (Awa doshuwa) ከሰዓት፣ (Awa wulaa) ጸሐይ ግባት፣ (Omarssaa) ማምሻ፣ (K'ammaa) ማታ፣ (Bilahiya) ሌሊት፣ (Hekka bilahiya) እኩለ ሌሊት፣ (Wonttumaatsaa) ሊነጋጋ ሲል በማለት፣ እንዲሁም አንድን ዓመት ከመስከረም እስከ ጥቅምት ድረስ ያለው አድሊያ (Adilliya woy Ofintsaa)፣ ከህዳር እስከ የካቲት በጋ (Boniya)፣ ከመጋቢት እስከ ግንበት አሱራ (Assuuraa)፣ ከሰኔ እስከ ጳጉሜ ድረስ ክረምት (Balgguwa) በሚል በተለያዩ ጊዜያት ከፋፍለው የሚቆጥሩት መሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

ቶክ-ቤኣ የሚከበርበት ወቅት ሲደርስ ተጣልቶ ማክበር የማይቻል መሆኑንና የተጣላም ካለ በሀገሩ ባህል መሠረት ከበዓሉ ቀድሞ የማስታረቅ ሥራ እንደሚሠራ፣

በቶክ-ቤኣ በዓል ቀን ዋዜማ ላይ አባወራ ካለ አባወራ፣ አባወራ ከሌለ የቤት ታላቅ ልጅ ችቦ በመያዝ ቤቱን ሙሉ እየዞረ የቤቱን ምሰሶ፣ የከበብት ግድግዳና የቤቱን በርና መስኮት እየነካካ ክፉ መንፈስ ይውጣ፣ የአሮጌ ዓመት ችግር፣ ማጣት፣ በሽታ፣ ጥላቻ፣... ከቤቴ፣ ከልጆቼ፣ ከእንስሳት፣... ውጣ! እያለ፣ አዲሱ ዓመት ለቤተሰቡ፣ ለእርሻዉ፣ ለከብቶቻቸው፣ ለጎረቤቱና ለሀገሩ ሁሉ የሰላም፣ የጤናና የጥጋብ እንዲሆን በመመኘት ከመረቀ በኂላ የአሮጌው አመት ከነችግሩ ማለፉን ለማመልከት በእጁ የያዘውን እሳት ውጪ አውጥቶ በመወርወር አሮጌው ዓመት ማለፉንና አዲሱ ዓመት መግባቱን በማብሰር ትዕምርት የሚከበር መሆኑን መረጃው አመላክቷል፡፡

ለቶክ-ቤኣ ልዩ ልዩ ባህላዊ ምግቦች ከተለያየ ዓይነት ምርቶች ተዘጋጅተው ማክበር የማይቀር ባህል መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

ልጃገረዶች ጣቶቻቸውን እንሶስላ (Wosolluwa) ተቀብተውና አዲስ ልብሶቻቸውን ለብሰው፣ ወንድ ልጆች ደግሞ አዲስ ልብሶቻቸውን ለብሰው ቤት ለቤት እየዞሩ የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን እየዘፈኑ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክቶቻቸውን አበባ እየሰጡ እንደሚገልጹ ከተጠኚዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 5.3. አስተያየት

ከጥናቱ ውጤት የዳውሮ ብሔረሰብ በየዓመቱ ቶክ-ቤኣን (አዲሱን ዓመት) ሲያከብሩ ከበዓሉ ጋር የማይነጣጠሉ በርካታ ባህላዊ እና ማህበራዊ እንዲሁም ትዕምርታዊ ጉዳዮች የሚከወኑ መሆናቸውን አስተውያለሁ፡፡ እነዚህ ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ትዕምርታዊ ክዋኔዎች ለብሔረሰቡ ትልቅ ትርጉም ያላቸውና ማህበራዊ ትስስራቸውንም ከመጠበቅ ረገድ የጎላ ድርሻ ያላቸው መሆኑንም የተገኘው መረጃ አመላክቷል፡፡

ስለሆነም በዓሉ ሲከበር ከበዓሉ ጋር ተያይዘው ያሉ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች የበለጠ የመስፋት እድል ስለሚኖራቸው በዓሉ ባህላዊ ይዘቱን ይዞ እንዲከበር የሚመለከታቸው አካላት ተገቢ ትኩረት ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል፡፡

የዳውሮ ብሔረሰብ በዓሉን ለማክበር በቅድሚያ የተጣላ ካለ ማስታረቅ ቀዳሚ ሥራ መሆኑንና በዓሉ ሰዎች በጋራ የሚያከብሩት በዓል መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ዘንድ የሚከወን የእርቅና የአንድነት ሥራ ለሀገር አንድነትና

ሠላም ሚናው በጣም የጎላ ስለሚሆን የአካባቢው አስተዳደር ማህበረሰቡን የማበረታታት ሥራ ቢሠራ የተሻለ ይሆናል።

ስለቶክ-ቤኣ ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች ያለመኖራቸው በመረጃ መሰብሰብ ሥራ ወቅት ትልቁ ችግር ነበር፤ ስለሆነም የበዓሉ ክዋኔ በጥናት በሳይንስ የተደገፈ እንዲሆን የአካባቢው ምሁራን ተጨማሪ የጥናት ሥራዎችን በተለይ ማህበረሰቡ ለበዓሉ ካለው አመለካከት አንጻር ቢሠሩ ይበልጥ ባህሉን እንዲጠበቅ ያደርጋል የሚል እምነት አለኝ።

ቶክ-ቤኣ ምንም እንኳ ከባዕድ አምልኮ ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያሳየ ቢሆንም አንዳንድ ግለሰቦች ከባዕድ አምልኮ ጋር በማገናኘት ባህላዊነቱ ላይ ተጽዕኖ እያሳደሩ እንዳሉ መረጃ ሰጪዎች ተቁመዋል። ስለሆነም ቶክ-ቤኣ ከየትኛውም ባዕድ አምልኮ ነጻ መሆኑን ለማህበረሰቡ ተገቢ የማስተወቂያ ቢሠራ የተሻለ ይሆናል።

የቶክ-ቤኣ በዓል ባህላዊ ቅርጹን ይዞ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ በተለይ ከተለያዩ ሰነድና መዛግብት እየተፈተሹ በሚመለከታቸው አካላት በኩል ለማህበረሰቡ ተገቢ ግንዛቤ ቢሰጥ የተሻለ ይሆናል።

ቶክ-ቤኣን በዓለም የባህል፣ የቅርስና የታሪክ መዝገብ (UNSCO) የማስመዝገብ ሥራ ቢሠራ ባህሉን ከብሔሩ አልፎ በሀገር ደረጃ የማስታወቅ እድሉ ከፍተኛ ስለሚሆን ቅድሚያ ተሰጥቶ ቢሠራ የተሻለ ነው የሚል አስተያየት አለኝ።

## ዋቢ ጽሑፎች


ለማ ንጋቱ፡፡ (2006)፡፡ የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሒውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ ፕሮግራም፤ በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የተሠራ ጥናት፤

ማሞ ተሰማ፡፡ (2007)፡፡ የዳዉሮ ሕዝብ ታሪክ እስከ 1983 ዓ.ም፡፡ ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፤

ሰለሞን ተሾመ፡፡ (2007)፡፡ የፎክሎር ምንነትና የጥናቱ ትኩረት አቅጣጫ፡፡ አዲስ አበባ፤ ፋርኢት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት፤

በዳውሮ ዞን ባህል ቱሪዝም መንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ የታተመ ዓመታዊ መፅሔት፡፡ (2003)፡፡ ዎንታ ቁ .7

በዳውሮ ዞን ባህል ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ፡፡ (2013)፡፡ 'ቶክ-ቤዓ' የዳዉሮ ብሔረሰብ ባህላዊ የዘመን መለወጫ በዓል ክስተትና አከባበር በዳውሮ ዞን ባህል ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ ተዘጋጅቶ ለወረዳ ባ/ቱ/ስ/ጽ/ቤት ሀላፍዎች ለ'ቶክ-ቤዓ' በዓል በወረዳ ደረጃ ለፓናል ውይይት እንድቀርብ ተዘጋጅቶ የቀረበ

ታደሰ ገብረኪዳን፡፡ (2000)፡፡ የኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር ታሪክ፡፡ ኦታዋ፣ካናዳ፡፡

አለም እሸቱ፡፡ (2001)፡፡ መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ፡፡ አድስ አበባ ቅድስት ማርያም ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋካልቲ፡፡

አስፋው አባተ (2013) የኢትዮጵያዊያንና የጎርጎሮሳዊያን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት ምንጭ፡ የሄኖክን የብርሀናት ነገር እና ባሕረ-ሀሳብን ተተኳሪ ያደረገ ጥናታዊ ዳሰሳ በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፤ የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ፤ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል፤ የሥነጽሑፍና ፎክሎር ለድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የተካሀሄደ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ (ያልታተመ)

አድማሱ አበበ፡፡ (2008)፡፡ የዳውሮ ታሪካዊ ቅርሶች (ያልታተመ)

ወንድሙ ከበደ፡፡ (2008)፡፡ ስልቻ ነጂዎች፤ አዲስ አበባ፡፡

ወንድሙና ሌሎቹ። (2012)። የዳዉሮ ብሔረሰብ የዘመን መለወጫ /Tookki Be'a /በዓል አከባበር ለፓናል ዉይይት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፤

ዘሪሁን አስፋው። (1996)። የስነ-ጽሑፍ መሰረታዊያን። አዲስ አበባ፤

ዩኒክ ኢትዮጵያ ቅ.2 ቁ.009 ። (2008) ። የዳውሮ ብሄር ባህላዊ እሴቶችና ትሩፋቶች። ሳንላይት ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ከዳውሮ ልማት ማህበር ጋር በመተባበር የታተመ መፅሔት፤

ያለው እንዳወቀ። (1998)። የምርምር መሠረታዊ መሪሆዎችና አተገባበር። ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤

------------ (2004)። የምርምር መሠረታዊ መሪሆዎችና አተገባበር። ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤

ዲያቆን ዘአማኑኤል አንተነህ። (2009)። የኢትዮጵያ በዓላት የሚል መጣጥፍ (ያልታተመ)

ጌጡ ተመስገን። (2012)። ቶክ-ቤኣ የዳውሮ ዘመን መለወጫ በሚል የተዘጋጀ መጣጣፍ (ያልታተመ)፤

ዓዲቁ። (2007)። የዳውሮ ብሄረሰብ ታሪክና ባህል። አልፋ አሳታሚ። 2ኛ እትም።

ፈቃደ አዘዘ። (1991)። የስነ-ቃል መምሪያ። ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት ተቋም። አዲስ አበባ።

Alan Longstaff (2005) Calendars from around the world , © National Maritime Museum.

Daimo, Desta D. (2020). Tookibe'a- The Cultural Event Of New Year Celebration Among the The Dawuro, South West Ethiopia. Hawassa University, College of Social science, Anthropology Department.

Dorsone, Richard M.(ed.) .(1972) . Folklore and Folkiif: An Introduction Chicago And London: The University Of Chicago Press.

Kotack, Tuifts H. (2010). Non-material cultures. Longman Inc.

Marsha ll, Douglas A. (2002). "Behavior, Belonging, and Belief: A Theory of Ritual Practice." Sociological Theory, Vol. 20, No.3.

Morris, Ian. 1992. Death Ritual and Socia l Structure in Classical Antiquitv 3rd ed. New York: Cambridge University Press,

Newsela Staff. (2016). The History of New Year's Eve.

Roth, Andrew L. 1995. ""Men Wearing Masks": Issues of Desc ription in the Analysis of Ritual." Sociological Theory, Vol. 13, No. 3.

Seid Ahmedi. (2007). A Historical Survey of Dawuro, Southwest Ethiopia (Up to 1974). (MA), Addis Ababa University.

Sims, Martha C., and Martine Stephens. (2005). Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Tradition. Logan: Utah State Uni versity Press.

The Ethiopian Messenger 17 - August-October 2020." **መጣጥፍ (ያልታተመ)፤**

# አባሪዎች

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

**ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ**

የዚህ ቃለ መጠይቅ ዓላማ የዳውሮ ብሔረሰብ የቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል የክወና ስርዓት ትንተና በሚል ርዕስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት የሚረዳን መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም እርስዎ የሚሰጡት ትክክለኛ መልስ ለጥናቱ ዓላማ ስኬት ትልቅ ሚና ስላለው ጥያዌዎችን በመመለስ እንድትተባበሩኝ በትህትና እየጠየቅሁ ይህን መጠይቅ በመመለስ ስለተባበሩኝ በቅድሚያ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

**ክፍል አንድ፤**

**የትውውቅ ክፍል፤**

**መመሪያ፡- ቀጥሎ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡**

1. ሥም፡--------------------------------------
2. ጾታ፡----------------
3. እድሜ፡--------------
4. የትምህርት ደረጃ፡------------------
5. የሥራ ድርሻ፡--------------------------
6. የመኖሪያ አድራሻ፡--------------------

**ክፍል ሁለት፤**

**ከቶክ-ቤኣ (የዳውሮ ዘመን መለወጫ) ጋር የተገናኙ መጠይቆች፤**

**መመሪያ፡- ቀጥሎ የቀረቡት መጠይቆች ከቶክ-ቤኣ በዓል አከባበር ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ በመጠይቆቹ መሠረት ትክክለኛ ሀሳብን ይግለጹ፡፡**

1. ቶክ-ቤኣ ማለት ምን የሚል ትርጉም እንዳለው ቢያብራሩ፤
2. በዳውሮ ብሔረሰብ ዘንድ ቶክ-ቤኣ የሚከበረው መቼ ነው? ለምን?
3. የቶክ-ቤኣ (ዘመን መለወጫ) በዓል ለዳውሮ ብሔረሰብ ያለው ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳ ምንድነው? ቢያብራሩ፤
4. በቶክ-ቤኣ በዓል ወቅት የሚከወኑ ክዋኔዎች ትርጉማቸው ምን እንደሆነ ቢገልጹ
5. የቶክ-ቤኣ በዓል በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ትዕምርታዊ ትርጉም ምን እንደሆነ ማብራሪያ ቢሰጡ፤
6. የዳውሮ ብሔረሰብ ለቶክ-ቤኣ በዓል የሚያከናውናቸው ተግባራት ምን ምን ናቸው?
7. ቶክ-ቤኣን ለማክበር የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች ምን ምን ናቸው? ከመቼ ጀምሮ ይደረጋሉ?
8. ለቶክ-ቤኣ በዓል የሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች የትኞቹ ናቸው? እንዴትስ ይዘጋጃሉ? እነዚህ ምግቦች በቶክ-ቤኣ በዓል አከባበር ወቅት ብቻ ይዘጋጃሉ?
9. የቶክ-ቤኣን በዓል ከሌሎች ሀገራት ዘመን መለወጫ ጋር የሚያመሳስል ነገር አለው? ካለ ምንድነው?
10. የቶክ-ቤኣ በዓል ባህላዊ ቅርጹን ይዞ ለትውልድ እንዲተላለፍ ምን ዓይነት መልዕክት ያስተላልፋሉ?

***አመሰግናለሁ!***

## አባሪ ሁለት፡- ከመረጃ ሰጪዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎች፤

የመረጃ አቀባዮች ዳራ

| ተ/ቁ | ሥም | ጾታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | የመኖሪያ አድራሻ | የሥራ ሀላፊነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢራሻ ደስታ ጦፋ | ወንድ | 71 | 6ኛ | ገና | የአካባቢ ባላባት |
| 2 | አቶ ዱባ ላሞሬ | ወንድ | 68 | መ/ትም/ት | ገና | ታወቂ ሽማግሌ |
| 3 | አቶ ዶግሶ ዶልኣሞ | ወንድ | 70 | መ/ትም/ት | ገና | ታወቂ ሽማግሌ |
| 4 | ወ/ሮ አጸዴ ዳርጩ | ሴት | 78 | - | ገና | የቤት እመቤት |
| 5 | ወ/ሮ ፋልታም ኮፎሌ | ሴት | 73 | - | ገና | የቤት እመቤት |
| 6 | አቶ ታዬ ግንባቶ | ወንድ | 45 | ድግሪ | ታርጫ | የዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ |
| 7 | ወ/ሮ አዲሴ ዘለቀ | ሴት | 39 | ሁለተኛ ድግሪ | ታርጫ | የዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ |
| 8 | አቶ መብራቱ ጳውሎስ | ወንድ | 35 | ሁለተኛ ድግሪ | ታርጫ | የዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ |
| 9 | ወ/ሪት ስንቅነሽ ደነቀ | ሴት | 28 | ድግሪ | ታርጫ | የዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ |
| 10 | አቶ ዘርሁን ተክሌ | ወንድ | 37 | ድግሪ | ታርጫ | የዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ |

## አባሪ ሦስት፦ የመረጃ ሰጪዎች ፎቶግራፍ



ኢራሻ ደስታ ጦፋ



አቶ ዱባ ላሞሬ



አቶ ዶግሶ ዶልኣሞ



ወ/ሮ አጸዴ ዳርጩ



ወ/ሮ ፋልታም ኮፎሌ



አቶ ታዬ ግንባቶ (የዞኑ ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ)



ወይዘሮ አዲሴ ዘለቀ (የዞኑ ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ)



አቶ መብራቱ ጳውሎስ (የዞኑ ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ)





ወ/ሪት ስንቅነሽ ደነቀ (የዞኑ ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ)



አቶ ዘርሁን ተክሌ (የዞኑ ባህል ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ)

አባሪ አራት፡- አጥኚው በዞን ባህል ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ ተገኝቶ መረጃ ስለመሰብሰቡ ከመምሪያው የተሰጠ ማስረጃ፤



ቁጥር 1129/7-23

ቀን 11/08/2016

ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ጉዳዩ፡- መረጃ ስለመስጠት ይሆናል፤

ከፍ ሲል እንደተገለጸው ተማሪ **አፈወርቅ ማኖስ** በጅማ ዩኒቨርሲቲ "**የዳውሮ ብሔረሰብ ቶክ-ቤአ (ዘመን መለወጫ) በዓል ክወና ስርዓት ትንተና**" በሚል ርዕስ እያካሄደ ላለው ጥናታዊ ጽሑፍ አስፈላጊውን ትብብር እንድናደርግ ተጠቅሶ ከትምህርት ክፍላችሁ በተጻፈልን ደብዳቤ መሠረት ተማሪው በመምሪያችን ማለትም **በዳውሮ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ** ቶክ-ቤአ የዳውሮ ብሔር ዘመን መለወጫ ላይ ትኩረት ያደረጉ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካላትና ክፍል ሲሰበስብ ቆይቶ የተመለሰ መሆኑን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር!!

Head, Dawuro Zone

Department Office

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የዳውሮ ብሔረሰብ የ"Tookki Be'aa" (ዘመን መለወጫ) በዓል የክወና ስርዓት ትንተና በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ሲሆን የራሴ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መደረጋቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- አፈወርቅ ማኖሶ ፊርማ፡-______________ ቀን፡- ______________